

አማራ ኮሙኒኬሽን ቢሮ

# ሐዲስ

20ኛ ዓመት ቁጥር 66

መስከረም ወር 2018 ዓ.ም



**በዓለም አቀፍ ተሞክሮ የጎብኝን ቁጥር ከፍ ለማድረግ ወሳኝ ከሆኑ ነገሮች አንዱ የ“ሰላም” ጉዳይ ነው፡፡**

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመንግስት ኮሙኒኬሽን ቢሮ

## ራዕይ

በመረጃ የበለፀገ፣ ሁለገብ ተሳትፎ የሚያደርግ፣ በመሠረታዊ ክልላዊና አገራዊ ጉዳዮች መግባባት የፈጠረ ህዝብ በ2022 እውን ሆኖ ማየት

## Vision

To see a society with rich information and all rounded active participation for a better understanding on fundamental regional and country level affairs for having common consensus in 2030

## ተልዕኮ

በመንግስት ኮሙኒኬሽን ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ መሪ ሚና በመጫወት በህብረተሰቡ መካከል ውጤታማ የመረጃ ልውውጥ በማድረግ በመሰረታዊ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች ዙሪያ የመላውን ህዝብ ግንዛቤ በማዳበር ሁለንተናዊ እድገታችንን ወደ ላቀ ደረጃ በማሸጋገር ለራዕያችን ስኬታማነት የተቀናጀ ርብርብ ማድረግ፣

## Mission

playing a leading role in government communication information for a successful information exchange with in a society. to enhance the awareness of the people on the fundamental government policies strategies. plans and programs for a better step of succession our vision by stron collaboration.

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመንግስት ኮሙኒኬሽን ቢሮ በየ 3 ወሩ የሚዘጋጅ መጽሔት

የመስከረም ወር 2018 ዓ.ም

20ኛ ዓመት ቁጥር 66

# ሐዲስ

**አዘጋጆች**

- ህያው ተስፋዬ
- ይበልጣል መኮነን
- ሲሳይ ጌቴ
- ደፋሩ እምሬ
- ሳሮን ስማቸው

**አርታኢ**

- ጋርዳቸው አንሙት
- ፈቃዱ ገድፍ አስናቀ

**ህትመት ስርጭትና ክትትል**

- ደባሱ ካሣ

**ግራፊክስ ዲዛይን**

- ጌታሁን ላቀ

ገጽ

መልዕክቶች፡-

ደብዳቤዎች፡-

**ፖለቲካ/መልካም አስተዳደር፡-**

**ፍትህን በተግባር** ........................................ 7

**ልማት/ኢኮኖሚ፡-**

**ከትናንት ዝና ወደ ነገ ተስፋ!** ........................ 12

**ባህል/ ታሪክ፡-**


**ጎብኝና መዳረሻው** ........................................ 17

**ማህበራዊ፡-**

የሰዓታት የሞት ድግስ........................................ 21

**ልዩ ልዩ**

**ዳግም ልደት የሚሻው ጥበብ** ........................ 26



ውድ  አንባቢያን መጽሔታችንን በማንበብ  አስተያየታችሁንና መልዕክቶቻችሁን በሚከተሉት አድራሻዎቻችን ይላኩልን

Facebook- Amhara Communications

ኢሜል- anrsnproduction@ gmail. com

ዩቲዩብ- Amhara Communications

ቲውተር-    @ANRSGCAO

ዌብሳይት- www.amharacomm.gov.et

ስልክ-  058 220 09 40 ፤ 058 226 5921፣ 058 220 4107

ፋክስ-  058 220 1105 / 058 226 4172

ፖ.ሣ.ቁ      607

የዝግጅት ክፍሉ



የተከበራችሁ የክልላችን ህዝቦች መንግስት የጀመራቸዉን የልማት እቅዶችና ፕሮግራሞች ዳር ለማድረስና የክልላችንንና የሀገራችንን ብልጽግና በማረጋገጥ የዜጎችን ሁለንትናዊ የልማት ተጠቃሚነት ከፍ ለማድረግ ከፍተኛ ርብርብ እያደረገ ይገኛል፡፡

በክልሉ የህዝቡን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል ትርጉም ያለው ሥራ ለሚሠሩና ድህነት ተኮር ለሆኑ ሴክተሮች በበጀት ድልድሉ ትኩረት እንዲያገኙ በማድረግ የተሠራ ቢሆንም ከአለው የልማት ፍላጎት ጥያቄ መስፋት አንጻር በዚህ ውስን በሆነው የመንግስት በጀት ብቻ የልማት ግቦችን ማሳካት አይቻልም፡፡ ነገር ግን ህዝቡ የልማቱ ቀጥተኛ ተሳታፊ የሚሆንበትንና የበኩሉን አስተዋጽኦ የሚያበረክትበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለብን፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ከተለያዩ የልማት አጋሮች የሚገኘውን የእርዳታና ብድር ሀብት ለታለመለት ዓላማና በወቅቱ ሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ  በትኩረት መሥራት ይኖርበታል፡፡ በራስ ገቢ ወጪን ለመሸፈን በትኩረት ከሚሠሩ ጉዳዮች አንዱና ዋነኛዉ ገቢ መሰብሰብ መሆኑ ታውቆ ለገቢ አሰባሰብም ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ፡፡

ከሁሉም በላይ ግን የክልሉን ልማት ለማፋጠንና የምንመኘውን የኢኮኖሚ እድገትና የዜጎችን ሁለንተናዊ ልማት ለማረጋገጥ የተመደበውን በጀት ወጪ ቆጣቢ፤ ውጤታማና ለታለመለት ዓላማ እንዲውል ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡ ይህም ሲባል በጀት ውስን ሀብት መሆኑን በመገንዘብና በህግና በሥርዓት የሚመራ መሆኑን መረዳት የበጀት አስተዳደር መርሆችን ተግባራዊ ማድረግ የግድ ነው፡፡ በመሆኑም የበጀት አጠቃቀማችንን በየጊዜዉ መገምገም፤ ብልሹ አሠራር እንዳይፈጠር ጥንቃቄ ማድረግ፤ የተጠያቂነት አሠራርም እንዲጎለብት ማድረግ የሚኖርብን ይሆናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የመንግስት ግዢን በእቅድ እንዲመራ ማድረግ፤ በፋይናንስ አጠቃቀም ህጋዊነት ኦዲት ወቅት የሚገኙ ግኝቶችን ፈጥኖ ማስተካከል ፤ የወጪ አስተዳደራችን የክልሉን የፋይናንስ አሠራር መርሆችን የተከተለ እንዲሆን ማድረግ እና የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ ጠንካራ እንዲሆን ማድረግ የሚጠበቅብን ነው፡፡

በአጠቃላይ የበጀት ዝግጅትና አስተዳደሩ ውጤታማ እንዲሆን በማድረግ፤ የወጪ አስተዳደሩንና ሂሳብ አያያዛችንን በማዘመን፤ የግዢና ንብረት አስተዳደር ሥርዓቱን የተቀላጠፈ እንዲሆን በማድረግና በበጀት አስተዳደሩ ላይ የፈጻሚና አስፈጻሚ አካላትን ተሳትፎ ከፍ እንዲል በማድረግ በበጀት ዓመቱ የታቀዱ የልማት ግቦችን ለማሳካት የተመደበውን በጀት ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመፈጸም መረባረብ የሁሉም አካላት ድርሻ መሆን አለበት ስል አሳስባለሁ፡፡

ጥላሁን  መሐሪ(ዶ/ር)

የአብክመ ገንዘብ ቢሮ ኃላፊ



በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ሪፎረም ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች ወስጥ አንዱ የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ነው፡፡ የአምራች ኢንዱስትሪው የአገር ኢኮኖሚን በመገንባት ሂደት በተለይ በምርቶች ላይ የፊትዮሽ እና የኋሊዮሽ ትስስር በመፍጠር፤የቴክኖሎጅ ሽግግር በማምጣት እንዲሁም ሰፊ የስራ እድል በመፈጠር ለኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ያለው አበርክቶ ከፍተኛ ነው፡፡

የክልላችን የዛሬ ኢኮኖሚ እና የነገ ብልጽግናን ከአምራች ኢንዱስትሪዎች መስፋፋትና ማደግ ውጪ ማሰብ አይቻልም። ሀገራት የለሙትና ያደጉት አምራች ኢንዱስትሪዎችን የትኩረት ማዕከል አድርገው በመስራታቸው ነው። የእኛም ሀገራዊና ክልላዊ ጉዞ ይህንኑ መስመር የተከተለ ነው። የኢንዱስትሪያላይዜሽን መስፋፋት የከተሞቻችንን ፈጣን እድገት ያቀላጥፋል። ከከተሞቹ መስፋፋትና ማደግ ጋር በሕብረተሰቡ የእለት ተእለት ኑሮ ውስጥም መሰረታዊ ለውጥ ያመጣል። የአኗኗር ዘይቤው ይቀየራል። የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን በመሳብ ሠፊ የሥራ ዕድል እየፈጠርን ጎን ለጎን የክልላችንን ገጽታ ለመቀየር ያስችለናል፡፡

የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉ የሚጠበቅበትን ሀገራዊና ክልላዊ የኢኮኖሚ ድርሻ እንዲወጣ ከኢንቨስትመንት መሳብ ጀምሮ ምርት ተመርቶ ለገበያ እስኪቀርብ ድረስ ባለው እሴት ሰንሰለት ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ መስራትን የሚጠይቅ ነው። ይህም የጋራ ቅንጅት በሚፈለገዉ ደረጃ ላይ ባለመሆኑ የክልላችን አምራች ኢንዱስትሪዎች ያሉባቸዉን ውስጣዊ እና ውጫዊ ችግሮች ባለመፈታታቸዉ ምክንያት ዘርፉ ካለው ዕምቅ አቅምና ክልላችን ለዘርፉ ካለው ምቹ ሁኔታ አንጻር እንደ ክልል ማግኘት የሚገባንን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም አግኝተናል ብሎ መደምደም አይቻልም፡፡ ባሉብን የማክሮ-ኢኮኖሚ ተግዳሮቶች እንዲሁም ባለፉት ዓመታት ካጋጠሙን ሃገራዊና ክልላዊ ሁኔታዎች ጋር ተያይዞ የብዙ ፋብሪካዎች ስራ ማቆም፣ የተጨማሪ ኢንቨስትመንት አለመስፋፋት፣ እና ምቹ የስራ ከባቢ አለመኖር በዘርፉ የተስተዋሉ ውስንነቶች ናቸው ፡፡ በእነዚህ መሰረታዊ ተግዳሮቶች የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ለኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግሩ የበኩሉን ሚና እየተወጣ ባለመሆኑ እንደ ሀገር በአስር አመት መርሀ ግብር የሚፈጸም ኢትዮጵያ ታምርት በሚል መሪ ቃል ሀገራዊ የንቅናቄ አቅጣጫ በክቡር ጠ/ሚኒስትር ዶር አብይ አህመድ አማካኝነት ተበስሯል፡፡

በክልላችንም ባለፉት ሶስት አመታት ባደረግናቸው የንቅናቄ መድረኮች ተስፋ ሰጭ ለውጦችን ማየት ጀምረናል። ለአብነትም በተለያየ ምክንያት ለረዥም አመታት ምርት አቁመው የነበሩ 480 አነስተኛ፤ መካከለኛና ከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች በአዲስ መልክ ወደ ማምረት ገብተዋል የአምራች ኢንዱስትሪው ከነበረበት 46 ነጥብ አራት በመቶ የማምረት አቅም 59 ነጥብ ሁለት በመቶ ደርሷል፡፡ በተለያየ ምክንያት ለረዥም ጊዜ ምርት አቁመው የነበሩ 301 አምራች ኢንዱስትሪዎች ችግሮቻቸው ተፈቶ ወደ ምርትና አገልግሎት ተመልሰዋል፡፡

የዘርፉን ማነቆዎች እየፈታን የመጣን ቢሆንም ዛሬም ቢሆን ዘርፉ በሚፈለገው ልክ እንዳይራመድ ያደረጉ የፋይናንስ አቅርቦት ፣ የመሰረተ ልማት ፍላጎት በተሟላ መልኩ አለመፈታት ፣ ሁሉንም የኢኮኖሚ ዘርፎች እየፈተነ ያለው ውስጣዊ የጸጥታ ችግሮችና የአገልግሎት አሰጣጣችን በሚፈለገው ደረጃ ላይ አለመድረስ የዘርፉ ፈተና ሆነው ቀጥለዋል፡፡ ሰለሆነም እነዚህን ማነቆዎች በመፍታት ረገድ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የራሳቸውን ድርሻ እንዲወጡ በቅንጅት መስራት ይኖርብናል፡፡

እንድሪስ አብዱ

የአብክመ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ኃላፊ

# ፍትህን በተግባር

በሲሳይ ጌቴ

ፍርድ ቤቶች ህግን የመተርጎም ህገመንግስታዊ ተልዕኮ የተሰጣቸው የመንግስት ሶስተኛ አካል ናቸው፡፡ ዲሞክራሲያዊ በሆነ የመንግስት ሥርዓት በህግ አውጪው የሚወጡ ህጎች በህግ አስፈጻሚው ይተገበራሉ፡፡ ከህግ ውጪ ተፈጽመዋል ለሚባሉ ድርጊቶች ደግሞ ፍርድ ቤቶች ህግንና ማስረጃን መሰረት በማድረግ በነጻነትና በገለልተኝነት ፍትህ(ዳኝነት) ይሰጣሉ፡፡ ሕዝብ በእነዚህ የመንግስት አካላት ላይ የጠነከረ እምነት ሲይዝ የህግ የበላይነት ይረጋገጣል፡፡ በውጤቱም የሃገርና የህዝብ ደህንነት ዋስትና ያገኛል፡፡ ሰላም ይሰፍናል፤ ፍትህ ይነግሳል፡፡

ለሃገር ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ እድገት ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ህዝቡንም ፍትሃዊ ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎች ይኖራሉ፡፡ የዳኝነት ስርዓቱን ወይም የፍትህ አሰጣጥ ሂደቱን ነጻ፣ ገለልተኛ፣ ቀልጣፋ እና ተገማች በማድረግ የህዝብ አመኔታን ለማትረፍ ዘርፈ-ብዙ የማሻሻያ ስራዎች መስራት አስፈላጊ ሲሆን ለፍርድ ቤቶች መዋቅር እና ለዳኝነት ስርዓት መሰረት የሆኑ የህግ ማዕቀፎችን በመፈተሽ ያሉባቸዉን ክፍተቶች እና ፍርድ ቤቱ ሊያደርጋቸው የሚችሉ እርማቶችን መለየት ቅድሚያ የሚሰጠዉ ተግባር ነዉ።

የፍርድ ቤቶችን ጫና የሚጨምረው ሌላኛው ሁኔታ በሁለት ወገኖች መካከል የሚከሰትን አለመስማማት ለመፍታት ሌሎች አማራጮችን ከመጠቀም ይልቅ በአብዛኛው ወደ ሙግት መግባት የተለመደ መሆኑ ነው፡፡ ሆኖም ፍርድ ቤቶችን የሚያጨናንቁ የተወሰኑ የጉዳይ ዓይነቶች በአስማሚ እገዛ በሁለቱ ወገኖች መካከል ስምምነት ሊፈጠርባቸው የሚችሉ ናቸው፡፡ ከሙግት ይልቅ በስምምነት አለመስማማቶችን መፍታት የፍርድ ቤት ሙግት ባለጉዳዮችን፣ ፍርድ ቤቶችንና ሃገርን የሚያስከፍለውን የጊዜ እና የገንዘብ ዋጋ የሚቀንስ ነው፡፡ በባለጉዳዮችም መካከል ሰላማዊ ግንኙነት ተጠናክሮ እንዲቀጥል የሚያደርግ ነው፡፡ በዚህ እሳቤ መሰረት በተወሰኑና አስቀድመው በህግ በተለዩ ጉዳዮች ላይ ለሙግት የሚመጡ ባለጉዳዮችን ለስምምነት በመመራት የፍርድ ቤቱን ጫና ለመቀነስ እንዲሁም በሁለቱም ወገን ያሉ ባለጉዳዮች ከፍተኛ ዋጋ ሳይከፍሉ የሚያስማማ ውጤት ላይ እንዲደርሱ ያስፈልጋል፡፡

የፍትህ ተቋማት ሚናቸው ይህ ሆኖ እያለ በወቅታዊ ሰላም መደፍረስ ምክንያት ከፍተኛ የሆነ ዋጋ ሲከፍሉ ይስተዋላል፡፡ በዚህም ውስጥ ሆነው የፍትህ ተደራሽነት እንዲኖር የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ሲያበረክቱ ይስተዋላል፡፡

የሐዲስ መጽሔት ዝግጅት ክፍልም የዛሬው ዝግጅቷን በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመገኘት የፍትህ አሰጣጥ ችግሮችና መፍትሔዎች ዙሪያ ከአንድ ባለጉዳይ እና ከጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕረዚደንት አማካሪ ከሆኑት ከአቶ ብኒያም ዮሃንስ ጋር ያደረግነው ቆይታ እንደሚከተለው አዘጋጅተነዋል፡፡ መልካም ንባብ!!

አቶ መዘምር ፈንቴ በምስራቅ ጎጃም ዞን እናርጂ እና እናውጋ ወረዳ ነዋሪ ሲሆኑ በፍትህ አሰጣጥ ዙሪያ ያጋጠማቸውን ገጠመኝና ቅሬታቸውን አጋርተውናል። እኝህ አባት ወደ አማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመጡት ለሶስተኛ ጊዜ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ በጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍትህ (የዳኝነት) አሰጣጥ ዙሪያ ቅሬታ እንዳላቸው ገልጸው ዋነኛ ችግራቸውም የቀጠሮ ቀን መብዛት እንደሆነ አስረድተዋል። "ለሶስተኛ ጊዜ መምጣቴ ላልተፈለገ የገንዘብ፣ የጊዜና የጉልበት ወጪ ዳርጎኛል" በማለት የገጠማቸውን እንግልት ገልጸዋል።

ይሁን እንጂ የዳኝነት አሰጣጡ ፍትሃዊ መሆኑን አምነው ችግሩን ለመፍታት ዘመናዊ አሰራሮችን መጠቀም እንደሆነ ጠቁመዋል። "ዘመናዊ አሰራሮችን መጠቀም ችግር ፈቺ በመሆናቸው በአካባቢያችን እንድንዳኝ ያስችሉናል" ያሉ ሲሆን በተለይም ከዚህ በፊት ይሰጥ የነበረው የፕላዝማ (የቪዲዮ ዳኝነት) አገልግሎት በተፈጠረው ግጭት ምክንያት በመቋረጡ አገልግሎቱን ማግኘት እንዳልቻሉ አስረድተዋል።

በመጨረሻም፣ አቶ መዘምር የሰላም አስፈላጊነትን አፅንኦት ሰጥተው፣ "ሰላምን በማስፈን ዘመናዊ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት የተፋጠነ የዳኝነትን ለሁሉም ተደራሽ በማድረግ የህብረተሰቡን እንግልት ማስቀረት ቢቻል" የሚል አስተያየታቸውን አካፍለዋል።

የሐዲስ መጽሔት ዝግጅት ክፍል የግለሰቡን ቅሬታ ጨምሮ የፍትህ አሰጣጥ ችግሮችና መፍትሔዎች ዙሪያ ከጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕረዚደንት አማካሪ ከሆኑት ከአቶ ብኒያም ዮሃንስ ጋር ቆይታ አድርገን የሚከተለውን ሃሳብ ይዘን ቀርበናል፡፡

በአማራ ክልል የእርስ በርስ ጦርነት ከጀመረ ውሎ አድሮ አመታት ተቆጥረዋል፡፡ ግጭቱም በሁሉም አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ ከፍተኛ ውድመት አስከትሏል፡፡ ልክ እንደ ሌሎቹ ተቋማት ሁሉ በፍትህ ስርዓቱ ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡ ባለ ጉዳዮች ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት ለመምጣት የአካባቢው ሰላም አለመሆን በፍትህ አሰጣጥ እና በስራ ሂደቱ ላይ እንቅፋት ፈጥሯል፡፡ በዚህ መንገድ በሁሉም ዞኖች፣ ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች ላይ የተሟላ ፍትህ ለመስጠት በሚያስችል ሁኔታ ላይ አለመሆናቸው የፍትህ ዘርፉን ጥያቄ ውስጥ ከቶት ቆይቷል፡፡

ግጭቱ አብዛኛው የክልሉን አካባቢ የሚሸፍን ስለነበር ጠቅላይ ፍርድ ቤትን ጨምሮ የዳኝነት አገልግሎት እንዳይሰጥ አድርጎታል፡፡ አልፎ አልፎ ከተወሰኑ አካባቢዎች በስተቀር በተፈጠረው ግጭት ምክንያት አገልግሎት መስጠት አቁሞ ነበር፡፡ አሁን ባለንበት ነባራዊ ሁኔታ ደግሞ አብዛኛው የክልሉ አካባቢዎች አንፃራዊ ሰላም መስፈኑን ተከትሎ የፍትህ አገልግሎቱን መስጠት ተጀምሯል፡፡



አቶ ብኒያም ዮሃንስ

የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፐረዚደንት አማካሪ

ማህበረሰቡ በዚህ የፀጥታ ቀውስ አልፎ ሲመጣ የተሟላ አገልግሎት ለመስጠት ፍርድ ቤቶች ራሳቸውን በሁሉም ዘርፍ ዝግጁ ማድረግ ይገባል፡፡ ስለሆነም ህብረተሰቡ ወደ ፍትህ ተቋማት መጥቶ የተሳለጠ አገልግሎት እንዲያገኝ የተለያዩ ተግባራት ማከናወን ተችሏል፡፡ በዋናነትም ፍርድ ቤት መጥቶ መዝገብህ አልተመረመረም ተብሎ የሚመለስ ባለጉዳይ እንዳይኖር ነገሮች ሁሉ በጥንቃቄ ተይዘው ዳኞች ሙሉ ጥረት በማድረግ መዝገቡን በመመርመር ለቀጠሮ ዝግጁ ማድረግ ነው፡፡ የሰበር ሰሚ አጣሪ ችሎት መዝገቦችን መርምሮ ያስቀርባል ወይም አያስቀርብም ብሎ ውሳኔ ለመስጠት ከአምስት እስከ ስድስት ወር ቀጠሮ ይሰጥ ነበር፡፡

ይህን የተንዛዛ አሰራር በአሁኑ ወቅት ደግሞ ባለጉዳዮች ወደ ተቋሙ በመጡበት እለት መዝገቡ ተመርምሮ ቅሬታ ማስቀረብና አለማስቀረቡ ተገምግሞ በአንድ ቀን ጉዳያቸውን ፈፅመው የሚመለሱበት ሁኔታ ተመቻችቷል፡፡

ፍትህ ፈልገው ወደ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሲመጡ በመንገድ በጣም በርካታ ችግሮችን አልፈው ነው፡፡ ያን ችግር ሁሉ አልፎ የመጣ ባለጉዳይ እዚህ ሲደርስ ሌላ ችግር ሊፈጠርበት አይገባም፡፡ በአግባቡ ህግንና ማስረጃን መሰረት አድርጎ በመጣበት አግባብ ለተጨማሪ እንግልትና ወጭ በማያስከትል አግባብ ተስተናግደው መመለስ ይገባቸዋል የሚል መርህ ይዘን እየሰራን እንገኛለን፡፡ ተጨማሪ ጊዜና አቅም የሚጠይቅ ቢሆንም ያለንን አቅም ሁሉ አሟጠን በመጠቀም ዳኝነቱን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ መስጠት ይገባል፡፡ ከአድሎና ወገንተኝነት በፀዳ መልኩ አስቸኳይ እና የተፋጠነ ፍትህ መስጠት ይጠበቃል፡፡

አንድ ባለ ጉዳይ ወደ ሰበር ሰሚ ችሎት ሲመጣ ይዞት የመጣው መዝገብ ተመርምሮ ጉዳዩ ወደ ዳኝነት የሚያስቀርብ ሆኖ ሲገኝ መደበኛ የዳኝነት ስርዓቱን ይከተላል፡፡ ስለዚህ መጥሪያ ከመስጠት የሚጀምር ሲሆን ሌላኛው ተከራካሪ መብቱና ሃሳቡ መደመጥ ስለሚኖርበት ወደ ተቋሙ በመምጣት ክርክሩ ይቀጥላል፡፡ ሆኖም በቀጣይ አስፈላጊውን የማጥራት ስራ ለማከናወን እና ይህን ሁሉ ሂደት ለማለፍ ቢያንስ ሶስት ጊዜ ቀጠሮ ያስፈልጋል፡፡ ማለትም መጥሪያ ማድረስ፣ ክርክር ማድረግ እና ለምርመራ መቅጠር ናቸው፡፡ በዚህ ምክንያት የሚፈጠርን ምልልስ አንዳንዶች የፍትህ መጓተት ነው ብለው ያስባሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህን መርሆች ትክክለኛና ህግ ያስቀመጣቸው ጉዳዮች መሆናቸውን ሁሉም አካላት ሊያውቃቸው ይገባል፡፡

የሚነሱ ቅሬታዎች ልክ ሊሆን የሚችለው ከሶስት ጊዜ በላይ እየተመላለሱ መዝገቡ ወይም ፋይሉ አልተመረመረም ከሆነ ጊዜን፣ ገንዘብን እና ጉልበትን ኪሳራ እንደሚዳርግ ተገንዝቦ ተቋሙ ትክክለኛ ውሳኔ ሊሰጥ ይገባል፡፡ ባለጉዳዩ የተሰጠውን መጥሪያ በአግባቡ ማድረስ ካልቻለ ድጋሚ መጥሪያ ሊወስድ ስለሚችል የፍትህ ስርዓቱን ሊያራዝም ይችላል፡፡ ከፍርድ ቤቶች ግዴታ አንፃር ግን ክርክሩ ከተጠናቀቀ መመርመር ባለበት ጊዜ መመርመር ተገቢ ነው፡፡ ከአቅም በላይ በሆነ ጉዳይ በስራ መብዛት ምክንያት የችሎት ሂደቱ አውቆት አልተመረመርም ተብሎ አንድ ቀጠሮ የሚሰጥበት አግባብ ሊኖር ይችላል፡፡

የዳኝነት ነፃነት ከጸጥታ መደፍረስ ጋር ተያይዞ ትልቅ አደጋ ገጥሞታል፡፡ ከፀጥታ ችግሩ ጋር በተያያዘ ዳኞች በሚወስኑት ውሳኔ ከችሎት ላይ እየተነሱ የሚታሰሩበት እንዲሁም የሚወስኑት ውሳኔ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡ ህብረተሰቡ በፍትህዊነት እና በነፃ ዳኝነት ያለውን እምነት የሚሸረሽር ሁኔታም ፈጥሮ ነበር፡፡ ዳኞች ተረጋግተውና ነፃ ሆነው ውሳኔ እንዳይወስኑ የሚያስችል ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ይህ የዳኝነት ነፃነት የሚገፈፈው በሁለቱም ወገን ማለትም በመንግስት የጸጥታ አካላትና በታጣቂው ሃይል ነው፡፡ ታጣቂ ሃይሉ ወደ ከተማ ሲገባ ፍርድ ቤቶችን ከመጉዳትና ከማውደም ባለፈ ዳኞች ላይ ከጸጥታ አካላት ጋር ግንኙነት አላችሁ በማለት ጉዳት አድርሰዋል፡፡ በተለይም ዳኞች ከሚሰጡት ውሳኔ ጋር ተያይዞ በሁለቱም ወገን እስራት፣ እንግልትና አካላዊ ጉዳት አስተናግደዋል፡፡

ከጸጥታ ችግሩ ጋር በተያያዘ የጸጥታ አካላት በዳኝነት ስራው ላይ በከፍተኛ ሁኔታ ችግር ሲፈጥሩ ይስተዋላል፡፡ ምክንያቱም በክልሉ ውስጥ



የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሎጎ

ያለው የመንግስት የፀጥታ ሃይል የተማከለ አለመሆኑ ነው፡፡ በክልሉ ውስጥ ያለው የጸጥታ አካላት የክልሉ ብቻ ሳይሆን የፌድራል መንግስቱ የፀጥታ መዋቅር ጭምር ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ አልፎ አልፎ የፖለቲከኛ ጣልቃ ገብነት ቢኖርም በአሁኑ ወቅት ለፍትህ ተቋማት ፈተና ሆኖ ሊነሳ የሚችል ግን አይደለም፡፡

በዋናነት በጸጥታ ሃይሉ የታሰሩ ሰዎችን ፍቱ ሲባሉ ያለመልቀቅ እና አድራሻ የመቀየር ሁኔታዎች ይከሰታሉ፡፡ እነዚህን ችግሮች መፍታት የሚቻለው ቅድሚያ ለሰላም መስጠት ሲገባ ነው፡፡ ሰላማዊ የመንግስት አስተዳደር ተመስርቶ በውይይት የሚፈቱበት ዜጎች በሰላም ወጥቶ የመግባት እና ፍትህ የማግኘት መብታቸውን በአግባቡ እንዲጠቀሙ እድል በመስጠት የዳኝነት ነፃነት እንዲተገበር መንግስት እና ህብረተሰቡ ጥላና ከለላ ሆኖ በጋራ መስራት ያስፈልጋል፡፡

ከዳኝነት ነፃነት ላይ የሚከሰቱ ችግሮችን ለመፍታት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የራሱን ህግ አዘጋጅቷል፡፡ ለአብነትም የዳኝነት ያለመከሰስ መብት ይገኝበታል፡፡ ይህም በህግ ጥበቃ የሚደረግበት ሲሆን የክልሉ ምክር ቤት ባደረገው መደበኛ ስብሰባ የፍርድ ቤቶች ማጠናከሪያ አዋጅ ላይ ዳኞች እጅ ከፍንጅ ካልተያዙ በስተቀር እንደማይታሰሩ ይደነግጋል፡፡

እንደ ክልል በፍትህ አሰጣጡ ዙሪያ የሚስተዋሉ ችግሮች አሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል የሙያ ስነምግባር፣ የእውቀትና የክህሎት ብቃት ክፍተቶች ናቸው፡፡ ፍርድ ቤቶች ከወረዳ ጀምሮ እስከ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ የሚዋቀሩት ስህተት መኖሩን ታሳቢ በማድረግ ስለሆነ በስራ ሂደት የሚጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት ነው፡፡ የአቅም ችግር በሁሉም ፍርድ ቤት የሚታይ ስለሆነ ተከታታይ በሆነ ስልጠና እና ግንዛቤ ፈጠራ የሚያድግና የሚስተካከል ነው፡፡

ሌላኛው ደግሞ የስነ ምግባር ችግር ሲሆን ተገልጋዮች የሚያሳዩት እና የሚጠቁሙት ችግር ነው፡፡ ይህን ብልሹ አሰራር ለመከላከል በጠቅላይ ፍርድ ቤት የተጀመሩ የሪፎርም ስራዎች አሉ፡፡ አስቀድመው ከተያዙና አሁንም ተግባራዊ ከሚደረጉ የሪፎርም ስራዎች ውስጥ አንዱ የባለሙያውን ስነምግባር ማሻሻል ነው፡፡ ይህን ችግር ለመፍታትና ተፈፃሚ ለማድረግ የባለሙያውን ስነ ምግባር ሊገዛና በአግባቡ ሊቆጣጠር የሚችል፣ ነፃነቱንና ገለልተኛነቱን በጠበቀ መልኩ ዳኝነት መስጠት በሚያስችል ሁኔታ የዳኞችና የጉባኤ ተሿሚዎች የስነ ምግባር ደንብ ተሻሽሎ በግንቦት ወር እንዲፀድቅ ተደርጓል፡፡ ይህ ደንብ ከአሁን በፊት በስነ ምግባር ደንቡ ያልተካተቱ አዳዲስ ነገሮችን ያካተተ ሲሆን በዋነኝነት የዳኞች የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም እና ቅሬታ አቀራረብ ስርዓትን አካቷል፡፡

ዳኞች ከፖለቲካዊና ከሃይማኖታዊ ጉዳዮች ነፃ ሆነው መታየት አለባቸው፡፡ ስለዚህ ይህን እምነት የሚሸረሽሩ በማህበራዊ ሚዲያ የሚተላለፉ ለብልሹ አሰራር መነሻና መንስዔ እንዳይሆኑ ለመቆጣጠር እና ለመከላከል የስነ ምግባር ደንብ ማካተት አስፈልጓል፡፡

በጠቅላይ ፍርድ ቤት ደረጃ ተግባራዊ የተደረገው የዲጅታላይዜሽን ስራ ብዙ ችግሮችን የሚፈታ ነው፡፡ ለአብነትም ህዝቡ በግልፅ ችሎት የመዳኘት ህገ መንግስታዊ መብት በየትኛውም አማራጭ ተጠቅሞ ከየትም ቦታ ሆኖ ምን ተሰራ ምን ተባለ ተብሎ ማየትና መረጃ ማግኘት አለበት ማለት ነው፡፡ የችሎቱን ተዓማኒነት ከፍ ከማድረግ ባለፈ የችሎቱንም ስራ ያቀለለ ነው፡፡ ምክንያቱም ተከራካሪው ያቀረበውን ሃሳብ እና ዳኛው የሰጠው ውሳኔ እና መነሻው ምንድን ነው የሚለውን እንዲከታተሉ ያደርጋል፡፡ ግልፅ ችሎት ማስቻል የብልሹ አሰራር ችግሮችን የሚቀርፍ ስለሆነ ዘመናዊ አሰራርን ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

ብልሹ አሰራር ውስጥ ተሳትፎ ካላቸው አካላት መካከል በብዛት ከጠበቆች ላይ ይነሳል፡፡ የጠበቆችን ጉዳይ የሚመለከተው የፍትህ ቢሮ ሲሆን የጋራ ውይይት በማድረግ ችግሮች መፍታት ተችሏል፡፡ ነገር ግን አብዛኛዎች ማስረጃ ስለሌለ የእርምት እርምጃ መውሰድ አልተቻለም፡፡ ማስረጃ የተገኘባቸውን ደግሞ በዲሲፕሊን እንዲጠየቁ እና ወደ ክስ ቀርቦ በሂደት ላይ ያሉ ባለሙያዎች አሉ፡፡ ከዳኞች ጋር በተያያዘ በአስተዳደር ጉባዔ ተከሰው ከስራ እንዲሰናበቱ ውሳኔ ተወስኗል፡፡ ለአብነትም በዚህ አመት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በየደረጃው በሚገኙ ዳኞች ዲሲፕሊን እንዲቀርቡ በሂደት ላይ የሚገኙ እና ቅጣት የተወሰነባቸው



"ፍትሃዊ ዳኝነት የህሊና እረፍት ነው!"

አሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ያሉበት ቦታ ለብልሹ አሰራር የተጋለጠ ከሆነ ቀድሞ ለመከላከል ያስችል ዘንድ ቦታ የመቀያየር ስራ ይሰራል፡፡ የቅጣት አላማው ሌሎችን ማስተማር ነውና ድርጊት የፈፀመው አካል ሌሎች እንዲማሩበት በማድረግ ከብልሹ አሰራር እራሰቸውን እንዲያቅቡ ያስችላል፡፡

እንደእኛ ሃገር ነባራዊ ሁኔታ ባህላዊ የዳኝነት ስርዓቱ ለዘመናዊ የፍትህ ስርዓት መሰረት ነው፡፡ ከ1950ዎቹ በፊት በባህላዊ የዳኝነት ህጎች ሲሰራ ቆይቷል፡፡ በአሁኑ ወቅትም አብዛኛዎቹ ጉዳዮች በተለይም በባልና በሚስት ግጭት በአስታራቂ ሽማግሌ ዳኝነት እንዲፈቱ ይደረጋል፡፡ ጉዳያቸውን በእርቅ እንዲፈታ በባህላቸውና በወጋቸው መሰረት እንዲጨርሱ ግፊት እንዲደረግ ህግና ስርዓቱ ይፈቅዳል፡፡ ከዚህ ባለፈ ደግሞ በፍርድ ቤት ወደ ክርክርና ዳኝነት ሂደቱ ከመግባታቸው በፊት አስማሚ ዳኛ ተመድቦላቸው ጉዳያቸውን በአስማሚው በኩል እንዲጨርሱ ጥረት ይደረጋል፡፡

ዘመናዊ የፍትህ ስርዓት ከባህላዊ ርቆና ለቆ መሄድ ስለማይችል የጋራ ግንኙነት አላቸው፡፡ ነገር ግን አሁን ባለው ሁኔታ ባህላዊ ህጎችና አሰራሮችን በፍትህ ብሄር ህጉ የመጨረሻው አንቀፅ ላይ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም ስለሚል በአግባቡ እየተተገበሩ አይደለም፡፡ ባህላዊ የዳኝነት ስርዓት ከጊዜ፣ ከገንዘብ፣ ከጉልበት ቆጣቢነት ባለፈ ለባለጉዳዮች አመች መሆኑ እና ወደፊት ከሚኖራቸው የግንኙነት ሁኔታ በባህላቸው መሰረት ቢጨረሱ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡

ኦሮሚያና ሲዳማ ክልል ባህላዊ ፍርድ ቤቶች አቋቁመው እየሰሩ ነው፡፡ ወደ ፍርድ ቤት የሚመጡ ጉዳዮችን ቀንሰው በመያዛቸው ለዘመናዊ የፍትህ ስርዓት ከገንዘብ፣ ከጉልበት እና ለወደፊት አስማምቶ ከመቀጠል አኳያ የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ እያደረገ ነው፡፡ በእኛ ክልል ባሕላዊ የፍትህ ስርዓት ህጋዊ እውቅና ባለመስጠቱ ምክንያት የሚጠበቀበትን የፍትህ ስርዓት እየሰጠ አይደለም፡፡ ሁሉንም ጉዳይ በፍርድ ቤት እንዲያልፍ ስለሚደረግ ፍርድ ቤት ላይ በከፍተኛ ሁኔታ የጉዳዮች መጨናነቅን ፈጥሯል፡፡ ሁለቱም ወገኖች በሚሰጠው ውሳኔ የማይረኩበት ሁኔታ ከመኖሩ ባሻገር የወደፊት ግንኙነታቸው ሰላማዊ እንዳይሆን እንቅፋት ይሆናል፡፡ ለዚህ ዋነኛው ምክንያት ደግሞ ባህላዊ የፍትህ ስርዓቱን በአግባቡ መጠቀም ባለመቻሉ ነው፡፡

ስለዚህ ባህላዊ የፍህ ስርዓትን ለመጠቀም እና ተግባራዊ ለማድረግ የባህላዊ ፍርድ ቤቶችን ማቋቋም እና እውቅና መስጠት ስላስፈለገ ረቂቅ ህግ ተዘጋጅቶ የክልሉ ምክር ቤት በአዋጅ ቁጥር 298/2017 አጽድቆታል፡፡ ስለዚህ ይህን አዋጅ ወደ መሬት ለማውረድ የሚስፈልገውን ህግ የክለሉ ምክር ቤት እንዲያወጣ ተደርጓል፡፡ ለባህላዊ ስርዓቱ እውቅና በመስጠት እና በጥናት ላይ በመታገዝ ከሰብዓዊ መብት ጋር የማይቃረኑትን በመለየት ጥቃቅንና አሉታዊ ጉዳዮችን እንዲያዩ በማድረግ ያግዛል፡፡

የፍትህ ስርዓት ዘምኗል ለማለት ዘመናዊነትን ከውጤታማነት ጋር ማስተሳሰር ያስፈልጋል፡፡ ለአብነትም የተቀላጠፈ፣ ህግና ስርዓትን መሰረት ያደረገ፣ ወቅቱን የጠበቀ በጣም ያልፈጠነ ያልተንዛዛም ፍትሃዊ የሆነ ውሳኔ ሲሰጥ ነው፡፡ ከግብዓት አንፃር ዘምኗል ለማለት ደግሞ የዜጎችን በነፃና በገለልተኛ ችሎት የመዳኘት መብት የሚያከብር አሰራር በመዘርጋት ባሉበት ቦታ ሆነው ክርክሮችን ማከናወን ሲቻል ነው፡፡

የዲጅታላይዜሽን አሰራርን በማጠናከር ድምፅን ወደ ጽሁፍ መቀየር የሚያስችል ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ዲጅታል መር የዳኝነት ስርዓትን (Smart Court System) ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ከግብዓት አንፃር ከፌደራል ፍርድ ቤቶችና ከኦሮሚያ ጋር ሲነፃፀር ወደ ኋላ የቀረ ነው፡፡ ለአብነትም ዲጅታል መር የዳኝነት ስርዓት (Smart Court System)፣ የቪዲዮ ዳኝነት (Video Conference) እና ድምጽን ወደ ጽሑፍ መቀየር(Audio Transcription) በፌድራልና ኦሮሚያ ክልል ላይ ተሟልተዋል፡፡ የአማራ ክልልም በዘመናዊነት ሲገለፅ ገና በሂደት ላይ ያለ ቢሆንም በተለይም ዲጅታል መር የዳኝነት ስርዓት (Smart Court System) ተዘርግቷል፡፡

የደንበኞችን እርካታ ለመጨመር ዘመናዊ አሰራርን መከተል ይገባል፡፡ ዘመናዊ አሰራርን ስንከተል ሊፈታው የሚችለው ችግር ደግሞ ምስክሮች ከሚሰጡት ቃላት ጋር የሚፈጠር ችግር እና ክህደትን ያስቀራል፡፡ ድምጽን ወደ ጽሑፍ




"ነፃና ገለልተኛ ፍትህ ለሁሉም!"

የሚቀይር አሰራር  መኖሩ የሰዎችን ድምፅ ወስዶ ወደ ፁህፍ ቀይሮ የምስክሩን ቃል በመውሰድ በድምጽና በጹህፍ በማቅረብ ትክክለኛ ውሳኔ እንዲሰጥ ያስችላል፡፡

በወቅታዊ ችግር ሁኔታ ውስጥም ሆኖ የሚመጡ ባለጉዳዮቹ መዝገባቸውን መርምሮ ማስረጃን መሰረት አድርጎ ውሳኔን በወቅቱ መስጠት ውጤታማ የሆነ አሰራር ነው፡፡ የፍርድ ቤት ውጤታማነት የሚለካው በሚከናወነው የዳኝነት አሰጣጥ ነው፡፡ ለአብነትም ወጪና ጊዜን ቆጣቢ የሆነ ፍትሐዊ የሆነ ውሳኔ ሲሰጥ ነው፡፡ ከወጭ አንፃር ሲታይም መዝገቡን አስከፍቶ ለሌላ ጊዜ ይሰጥ የነበረው ቀጠሮ በወቅቱ ተመርምሮ ተጨማሪ ምርመራ ሳያስፈልገው በዚያን እለት ውሳኔ ስለሚሰጥ እንግልት ይቀንሳል፡፡ ከወጭ፣ከጊዜና ከተለያዩ ስጋቶች ነፃ ማድረግ ውጤታማ አሰራርን ይገልፃል፡፡

የፍትህ ስርዓቱ ስራ በርካታ ባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎ ድምር ውጤት ነው፡፡ ከዳኝነት ነጻነት እና ገለልተኛነት ጀምሮ ውጤታማና የተቀላጠፈ ፍትሀዊ ወይም ተደራሽ የሆነ ውሳኔ እስኪመጣ ድረስ በርካታ ተሳታፊና ተዋናይ አሉበት፡፡ የዳኝነት እና የፍትህ አካላት የትብብር መድረክ በማቋቋም የፍትህ አካላት ደህንነት የተጠበቀ ሆኖ ጤናማና በትብበር መስራት የሚያስችልባቸው ስራዎች ላይ ተግባብተውና ተቀናጅተው ውጤታማ ስራ እንዲሰሩ የሚያስችል አደረጃጃት ተፈጥሯል፡፡ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ስር ሆኖ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ተቋቋሞ እየሰራ ይገኛል፡፡ በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ላይ ይነሳ የነበረውን የትብብር መድረክ በፍታብሄር እና በአስተዳደር ፍትህ ዘርፍ ላይ ፍርድ ቤት ብቻውን ውሳኔ ሊሰጥ አይችልም፡፡ ማስረጃ ሰጭ ተቋማት በሚገባ ማስረጃ መስጠት ስለሚጠበቅባቸው በትክክል መረጃ መስጠትና ከትክክለኛ እና ከእውነተኛ ፍትህ ጎን መቆም ይገባል፡፡

በመጨረሻም አቶ ቢኒያም መንግስታዊ ይሁን መንግስታዊ ያልሆነ ተቋም መረጃንና ማስረጃን በትክክለኛው ሰዓት እና ፍጥነት ለፍትህ ተቋማት በማድረስ ዘመናዊ አሰራርና ፍትሃዊነትን ለማስፈን ሁሉም አካላት በሚገባቸው ተግባራት ላይ ተግባብተው እና ተቀናጅተው መስራት ይገባል፡፡ መንግስት የዳኝነት ነፃነት እና ገለልተኝነትን የሚያከብር ህጎችን ከማውጣት በተጨማሪ የወጡ ህጎችን የማስፈጸምና የማስከበር ሃላፊነት በሚገባ በመወጣት በዳኝነት ስርዓቱ ላይ አመኔታ እዲኖረው በማድረግ በኩል ስራዎችን መስራት የሚገባው ሲሆን ተገልጋዩ ማህበረሰብ ነፃና ገለልተኛ ሆኖ በፍርድ ቤት የመዳኘት መብት ያላቸው መሆኑን አውቀው መብታቸውን በአግባቡ በመጠቀም ለብልሹ አሰራር መጋለጥ ሳይገባቸው ከህግና ከማስረጃ ውጭ በጉቦና በዘመድ ለመዳኘት ከፍተኛ ፍላጎትና አዝማሚያ ባለማሳየት በህግና በመመሪያው መሰረት ነፃ ዳኝነት ማግኘት ይገባል ሲሉ ሃሳባቸውን አካፍለውናል፡፡

አቶ መዘምርን እና አቶ ብኒያምን ለሰጡን ማብራሪያ እጅግ እያመሰገን ሶስት ጊዜ ቀጠሮ መስጠት ህጉ የሚፈቅደውና የተከሳሽ መብት መከበር ስላለበት እንደሆነ ታምኖ በፍትህ ስርዓቱ ላይ በክልሉ ውስጥ የተፈጠረው የሰላም እጦት ወይም የእርስ በርስ ጦርነት ከፍተኛ ችግር ከመፈጠሩ ባሻገር የህጎች ተፈፃሚነትና የዘመናዊ ስርዓት ተደራሽነት በማስፋት የዳኝነት ነፃነትን በማክበር ፍትህን ከወረቀት ባለፈ በተግባር ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ተደራሽ በማድረግ ክልሉ ፍትህ የሰፈነበት፣ ከአድሏዊ አሰራር የጸዳ፣ ነጻ እና ገለልተኛ አሰራርን ለሁሉም ማዳረስ አስፈላጊ መሆኑን በመረዳት መንግስት፣ ህብረተሰቡ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት የድርሻቸውን መወጣት እንደሚጠበቅባቸው የዝግጂት ክፍሉ መልዕክቱን ያስተላልፋል፡፡ ሰላም ለሁላችን!!!

# ከትናንት ዝና ወደ ነገ ተስፋ!

**በይበልጣል መኮንን**

የትናንት ገድሎቻችን የአብነት ማኅተም ፤ የዛሬው ጥረታችን የነገ ተስፋችን ዋልታ ነው! ኢትዮጵያችን የብዙ ታሪክ ፣ የበርካታ ባህልና ስልጣኔ ባለቤትነቷን እንዳስጠበቀች ዛሬም ያላትን ክብርና የጽናት መንፈስ በማሳየት ዓለምን እያስደመመች ትገኛለች፡፡ የቀደምት ስልጣኔዋ አሻራዎች ትናንትን ከዛሬ ፤ ዛሬን ደግሞ ከነገ ጋር እያስተሳሰሩ ድህነትን ታሪክ ለማድረግ እየተደረጉ ያሉ ጥረቶችና እየተገኙ ያሉት ድሎች ለዚህ ትልቁ ማሳያ ናቸው።

እንደ ማኅበረሰብ ዛሬ የሚያጋጥሙንን ፈተናዎች ተሻግረን የተሻለና ብሩህ ነገን መፍጠር የምንችለው በታሪክ ቁጭት ውስጥ ሆነን ሀገራችን ኢትዮጵያ በ"ይቻላል" መንፈስ ያቀደቻቸውን በርካታ አገራዊ የልማት እቅዶችን እውን ማድረግ ስንችል ብቻ ነው። በተለይም አሁን ያለንበት የእድገት የለውጥ ምዕራፍ የተጀመረው ለውጥ ትርጉም ያለው ፍሬ አፍርቶ ወደ ሁለንተናዊ እድገት እንዲሻገር የኢኮኖሚው ዘርፍ ሰፊ ስራ የሚያስፈልገውና ለእድገት መሰረት ተደርጎ የሚወሰድ የማዕዘን ድንጋይ ነው።

በዚህ ረገድ በኢትዮጵያ በኢኮኖሚው ዘርፍ የተሰሩ ስራዎችን ዋቢ ያደረጉ መረጃዎች እንደሚያመላክቱት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣቱን ነው። የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እድገት ከማሳየቱም አልፎ የመዋዕለ ንዋይ ፍላጎት ክፍተትን እየሞላ መሆኑን ዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም ባወጣው ሪፖርቱ በአፍሪካ ግዙፍ ኢኮኖሚ ካላቸው ሀገራት መካከል ኢትዮጵያን አንዷ እንደሆነች አመላክቷል።

ሀገራችን የራሷን ጸጋ አልምታ የሕዝቦችን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉድለትን በመሙላት ፤ ወቅታዊ ተጽእኖዎችን ተቋቁመው ለሀገሪቱ እድገት ወሳኝ በሆኑ ዘርፎች ላይ የተሰማሩ ድርጅቶችን በሀገርም ሆነ በክልል ደረጃ በማቋቋም ለኢኮኖሚ እመርታ ለውጥ እንዲያመጡ እየተሰራባቸው ነው። እንደ ሀገር የተቀመጠውን የእድገት ፍኖተ-ካርታ ግቦች እውን ለማድረግ በቢዝነስ እና በኢንቨስትመንት የተሰማሩ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በበርካታ ዘርፎች ተሰማርተው ለውጥ እያስመዘገቡ ይገኛሉ።

ከእነዚህ በኢኮኖሚው መስክ ተሰማርተው በከፍተኛ ደረጃ የሕዝብ ጥቅምን ከሚያጎለብቱትና በፍጥነት ለውጥ እያስመዘገቡ ከመጡት ድርጅቶች መካከል በአማራ ክልል የሚገኘው ንጋት ኮርፖሬት ከፍ ብሎ ከሚጠሩት መካከል አንዱ ነው። ንጋት ኮርፖሬት ከበርካታ የቢዝነስና ኢንቨስትመንት ሥራዎቹ ባሻገር ኮርፖሬቱ በማኅበራዊ ልማት ዘርፍ በተለይም በስራ እድል ፈጠራ፣ በማኅበራዊ ደህንነት እና አስቸኳይ ሰብዓዊ ድጋፍ ሥራዎቹ ይታወቃል።

በዚህ ረገድ ሀገራችን ኢትዮጵያ ከታሪካዊ ዝናዋ እስከ አሁን እያስመዘገበች ያለውን ድል በመደገፍ ንጋት ኮርፖሬት የዚሁ የልማት ጉዞ አካል ሲሆን የሀገርን ኢኮኖሚያዊ መሠረት በማጠናከርና የማኅበረሰብን ህይወት በማሻሻል የነገዋን ኢትዮጵያ ብሩህ ተስፋ ለመገንባት እያደረገ ያለውን ጥረት እና ለሕዝብ እያከናወነ ስላለው ሥራ ሐዲስ መጽሔት እንጋዳ ጋብዛ “ከትናንት ዝና ወደ ነገ ተስፋ” በሚል ርዕስ ያደረገችውን ቆይታ እንካችሁ ትላለች መልካም ንባብ፡፡

አቶ ውድነህ ገዛኸኝ የንጋት ኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ፕሪንሲፓል ኦፊሰር ናቸው፡፡ አቶ ውድነህ ንጋት ኮርፖሬት በአማራ ክልል ሕዝብ የልማት ጥረቶች ውስጥ ያለውን ጉልህ ሚና እንዲህ ይገልፁታል፡፡

ንጋት ኮርፖሬት በሕዳር ወር 1988 ዓ.ም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር ከ483-506 በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት የተቋቋመ ሲሆን በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መመዝገቢያና ማስተዳደሪያ አዋጅ ቁጥር 194/2004 ዓ.ም የተመዘገበ የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት ነው።

የንጋት ኮርፖሬት ዋነኛ መርሆዎች ግልጽነትና ተጠያቂነት ናቸው። ይህንን ለማረጋገጥም ተቋሙ ለአማራ ሕዝብ ተወካይ ለክልሉ ምክር ቤት ተጠሪነት አለው። ምክር ቤቱ የተቋሙን ስትራቴጂካዊ ዕቅድ የመገምገም፣ የማጽደቅ እና አፈጻጸሙን ሊያሳኩ የሚችሉ የንጋት ቦርድ አባላትን የመምረጥና የመሰየም ሥልጣን አለው።

ይህ አሰራር ንጋት የክልሉን ሕዝብ ፍላጎትና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች መሰረት አድርጎ እንዲንቀሳቀስ አስችሎታል፡፡

ከዚህ ቀደም የነበረው የንጋት ሎጎ የአማራ ሕዝብን ባህልና እሴት በሚገባ አይገልጽም ነበር። ከዚህም ባለፈ ድርጅቱ የሚሰራውን ስራና የወደፊት አቅጣጫ ግልጽ ባለማድረጉ ፣ እንዲሁም ለተሳሳተ ትርጓሜ ሲያጋልጥ በመቆየቱ ፣ ህብረተሰቡ በነባሩ ስያሜና ሎጎ ላይ ለረዥም ዓመታት የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲይዝ አድርጎ ነበር። ይህ ደግሞ ህብረተሰቡ የባለቤትነት መንፈስ እንዳይሰማው ችግር ሆኖ ቆይቷል። ይህን ችግር ለመቅረፍ እና የተቋሙን ማንነት በአግባቡ ለመግለጽ ሲባል አዲስ ስያሜና ሎጎ "ንጋት" በሚል ተመርጧል። አዲሱ ስያሜ ፣ ከዓላማ፣ ራዕይ ፣ ተልዕኮና እሴቶች አኳያ በቀለምና በቅርጽ ሕብር ሲተነተን ፣ "ንጋት" የሚለው ቃል የጠዋት ጮራን ፣ ከጨለማ ወደ ብርሃን መሸጋገርን ያመለክታል። ይህ ስያሜ ተቋሙ የአማራ ክልልን ወደ ልማትና ብልጽግና ለመምራት ያለውን ራዕይ በሚገባ የሚያንፀባርቅ ነው። አዲሱ ሎጎም የንጋትን ተስፋ ሰጪነትና እድገትን የማቀጣጠል ሚናውን የሚያሳይ ሆኖ የተቀረፀ ነው፡፡

ይህ ስያሜ ከተቋሙ አውድ ጋር ሲተነተን ነገን በተስፋ የሚያልም ወደ አንጸባራቂ ብርሃን መድረሻ ውክልና ያለው ነው፡፡ከአርማ አኳያ የቀለምና ቅርጽ ትንታኔውን ስንመለከት አረንጓዴው ቀለም ልምላሜን፣ ፍካትን፣ አዲስ ቀን መምጣትን መስከረም መጥባትን የሚያሳይ ቀለም ነው፡፡ ቢጫው ቀለም ደግሞ በቀለም ስነ-ልቦና (Colour Psychology) ሰላምን ፣ ግልጽነትን ፣ ደግነትንና የመሳሰሉትን አዎንታዊ ገጽን የያዘ ነው፡፡

ድርጅቱ የአማራ ክልል ህዝብ ሀብት መሆኑን በተደጋጋሚ ለማስረዳት ቢሞከርም የአብዛኛውን የማህበረሰብ ክፍል የተሳሳተ ግንዛቤ ለመቀየር ሳይቻል ቆይቷል፡፡ ስለሆነም የተፈጠረውን ብዥታ ግልፅ ለማድረግ እና በአዲስ መንፈስ ወደ ስራ ለመግባት ቀድሞ ይጠራበት የነበረውን ስሙን “ንጋት የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት” በሚል



አቶ ውድነህ ገዛኸኝ

አዲስ ስያሜና ሎጎ እንዲሁም ቀለማት መቀየር ተችሏል፡፡ በሎጎው ላይ የተነደፉት የቅጠሎች ብዛት ሰባት መሆናቸው ንጋት ሰባቱንም ቀናት ሀያ አራቱንም ሰዓታት በትጋት ከንጋት እስከ ሌሊት እንደሚሰራ ለማመላከት የተቀመጠ ነው።

ንጋት ኮርፖሬት የአማራ ክልልን የልማት ጥረቶች ለመደገፍ የተቀመጡትን ዋና ዋና ዓላማዎችና የሚከናወኑ ተግባራትን አስመልክቶ ንጋት ኮርፖሬት በጎ አድራጎትን ከዘላቂ ልማት ጋር በማጣመር የክልሉን ሕዝብ ሁለንተናዊ እድገት ለማረጋገጥ እየሰራ የሚገኝ ነው። በንጋት መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ ዘጠኝ ላይ እንደተመለከተው፣ የኮርፖሬቱ ዋና ዓላማዎቹ አንዱ በማህበራዊ ልማት ስራዎች ላይ በንቃት በመሰማራት የክልሉን ህዝብ መደገፍ ነው። ይህ ድጋፍ በተለይ ለህጻናት ፣ ለአካል ጉዳተኞች ፣ ለወጣቶችና ለሴቶች ማህበራዊ ልማት ትኩረት በመስጠት የሚከናወን ነው። ዓላማውም የክልሉን ህዝብ ማህበራዊ ህይወት የሚለውጡ ስራዎችን በመደገፍ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ ማድረግ ነው።

የገቢ ምንጮች ማስፋፋትና ሀብትን በመፍጠር ኮርፖሬቱ ገቢ በሚያስገኙ ፣ የአገልግሎትና የንግድ ተቋማት ውስጥ በመሰማራት ወይም ባለአክሲዮን በመሆን ተጨማሪ ሀብት እየፈጠረ ነው። በተጨማሪም አዳዲስ የንግድ ድርጅቶችን በብቸኝነት በመያዝ የክልሉን ልማት ለመደገፍና ለበጎ አድራጎት ዓላማዎች የሚውል ሀብት ማመንጨት ሌላው የንጋት ቁልፍ ተግባር ነው።

የቴክኖሎጂ ሽግግርና የሥራ ዕድል ፈጠራ ልዩ ልዩ የገቢ ማስገኛ ተቋማትን በማቋቋም ንጋት ኮርፖሬት የቴክኖሎጂ ሽግግርን ለማምጣት እየሰራ ነው። ይህም በክልሉ ውስጥ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች እንዲስፋፉ በማድረግ የምርታማነትን ደረጃ ከፍ ያደርጋል። ከዚህ ጎን ለጎንም፣ እነዚህን ተቋማት በመጠቀም ለክልሉ ነዋሪዎች በተለይም ለወጣቶች የሥራ ዕድሎችን በመፍጠር የኑሮ ደረጃቸውን ለማሻሻል አስተዋፅኦ የሚያደርግ ነው።

ንጋት ኮርፖሬት የክልሉን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት ለማፋጠን የሚደረገውን ጥረት በልዩ ልዩ ፕሮጀክቶች ይደግፋል። የአካባቢ ልማት ጥበቃ ስራዎችም የኮርፖሬቱ የትኩረት አቅጣጫዎች ውስጥ የሚካተቱ ናቸው። ይህም የአካባቢን ዘላቂነት በማረጋገጥ ለትውልድ የሚተላለፍ አስተማማኝ መሰረት ለመጣል ያለመ ነው።

የአማራ ክልል በኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴው የላቀ ደረጃ ላይ እንዲደርስ የበኩሉን አስተዋፅኦ እያበረከተ የሚገኘው የንጋት ኮርፖሬት በርካታ ኩባንያዎችን በአዲስ መልክ በማዋቀርና በማስተባበር የክልሉን ህዝብ የመልማት ፍላጎት እውን ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ነው። ይህ ኮርፖሬት በማኑፋክቸሪንግ፣ በግብርናና ፣ አግሮ-ፕሮሰሲንግ፣ በንግድ፣ በትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ፣ በኮንስትራክሽንና በማማከር አገልግሎት ዘርፎች በመሰማራት የክልሉን የኢንዱስትሪ ልማት እና የአገልግሎት ዘርፍ ለማነቃቃት እየሰራ ይገኛል።

የንጋት ኮርፖሬት አሁን ላይ በ28 ተቋማት ላይ የኢንቨስትመንት ሀብት መድቦ የሚያንቀሳቅስ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ በ16 ኩባንያዎችና በሁለት ፕሮጀክቶች ላይ ሙሉ በሙሉ የባለቤትነት ድርሻ ያለው ነው። በተጨማሪም በ10 ተቋማት (ሶስት አምራች ኩባንያዎች ፣ ዓምስት ፋይናንስ ተቋማት ፣ ሁለት የሚዲያና ህትመት ተቋማት) ላይ የአክሲዮን ድርሻ በመያዝ ኢንቨስትመንት እያካሄደ ይገኛል። ጥረት በባለቤትነት የያዛቸው ኩባንያዎች መካከል ጥቁር አባይ ትራንስፖርትና ትራንዚት ፣ አምባሰል የንግድ ስራዎች ድርጅት ፣ ጣና ኮሙኒኬሽን ፣ ጎንደር ብቅል ፋብሪካ ፣ ግዮን የፕላስቲክ ውጤቶች ማምረቻ ፋብሪካ ፣ ዋልያ ቆርኪ ፋብሪካ ፣ አዚላ ኤሌክትሮኒክስ ቢዲሲ ኮንስትራክሽን ፣ ገንዳ ውሃ የጥጥ መዳመጫ ፋብሪካ ፣ ቻግኒ የጥጥ መዳመጫ ፋብሪካ ፣ኤም.ቪ.አር. የአማካሪዎች ቡድን ፣ ስካይ ጋርመንት ፣ በከልቻ ትራንስፖርት አክስዮን ማህበር ፣ ባህርዳር ጨርቃጨርቅ አክስዮን ማህበር ፣ ኮምቦልቻ ጨርቃጨርቅ አክስዮን ማህበር እና የትመን ጅፕሰምና የጅፕሰም ውጤቶች ፋብሪካ ኃ/የተ/የግ/ማ ሲሆኑ እንዲሁም በፕሮጀክት ደረጃ ያሉ ኩባንያዎች የካርቶን ማምረቻ ፋብሪካ እና ማዕድ የምግብ ኮምፐሌክስ ፋብሪካ ይገኙበታል፡፡

በፋይናንስ በኩል የውጭ ምንዛሪ በማመቻቸት፣ የስራ ማስኬጃ ብድር በማቅረብ እና የትርፍ ህዳግን (profit margin) ለማሳደግ በሚረዱ ተግባራት ላይ ትኩረት ተደርጓል። በተለይም የዋጋ ተመንን (pricing policy) በተከታታይ ማሻሻል እና አዳዲስ ደንበኞችን በማፍራት የምርትና ሽያጭ መጠንን የማሳደግ ስራ ተከናውኗል። በተጨማሪም የወጪ ቅነሳ እና የሀብት አጠቃቀም ውጤታማነትን በማሳደግ በኩል ጉልህ አስተዋፅኦ አበርክቷል።

የኩባንያዎችን ገቢ ፣ የትርፍ ማርጂን እና የሀብት አጠቃቀም ለማሳደግ የገቢ ማሳደጊያ ስርአት መዘርጋት ፣ ከክምችት አስተዳደር ማሻሻያ ጋር ተያይዞ የአቅርቦትና ሎጅስቲክስ ስርአት ማዘመን ፣ ውጤታማ የሀብት አጠቃቀም እና የወጪ መቀነሻ እርምጃዎች የስትራቴጂው ቁልፍ አካል ናቸው። በዚህም መሰረት በስርአታዊ መሻሻያ ስትራቴጂ ትግበራ ውስጥ ያሉ ኩባንያዎች በምርታማነት፣ በሽያጭ፣ በገቢና በትርፋማነት ከፍተኛ መሻሻል አሳይተዋል።

በገበያ ማስፋት ረገድም ኩባንያዎች ነባር የገበያ ድርሻቸውን እንዲያሳድጉ ፣ አዳዲስ ገበያዎችንና ደንበኞችን እንዲይዙ ፣ አዳዲስ ምርቶችን ወደ ገበያ እንዲያስገቡ የፋይናንስ ፣ የቴክኖሎጂና የእውቀት ድጋፍ ተደርጓል። ከዚህም ባሻገር ምርታማነትን እና ትርፋማነትን በማሳደግ የክልሉን የገበያ ጉድለት መሙላት፣ ኪሳራን መቀነስ፣ የብድር አከፋፈል፣ የፕሮጀክቶች አፈጻጸም ፣ ገጽታ ግንባታ እና ማኅበራዊ ልማት ዘርፎች በኩል አበረታች ውጤቶች ተመዝግበዋል።

የሰው ሀብት ልማትን በተመለከተም ኮርፖሬቱ ለኩባንያዎች አመራርና ቁልፍ ባለሙያዎችን በማሟላት ፣ አደረጃጀቶቻቸውን በማስተካከል ፣ የአሰራር ስርአት የሚገነቡ መመሪያዎችን በማዘጋጀትና በማፅደቅ ውስጣዊ ግንኙነታቸውን በመፈተሽና መፍትሄ በሚሹት ላይ ድጋፍ በማድረግ የለውጥና የእድገት እንቅስቃሴን አፋጥኗል።

ከቢዝነስና ኢንቨስትመንት ባሻገር ኮርፖሬቱ በማኅበራዊ ልማት ዘርፍም ጉልህ ሚና እየተጫወተ ነው። በተለይም በስራ እድል ፈጠራ ፣ በማኅበራዊ ደህንነት እና በአስቸኳይ ሰብዓዊ ድጋፍ ስራዎች ለህዝብ የቀረበ የዘላቂ ልማት መሰረት እየሆነ መጥቷል። በወጣቶች ተጠቃሚነት ፣ በትምህርትና ጤና መሰረተ ልማት ፣ በንጹህ መጠጥ ውሃ ግንባታ ፣ በአስቸኳይ ሰብዓዊ ድጋፍ እና ለክልሉ ህዝብ ባህልና ስፖርት ማደግ በኩል የበኩሉን አስተዋፅኦ እያደረገ ነው።

ጠንካራ የፋይናንስ መሰረት በመፍጠር ረገድ ኮርፖሬቱ እስከ 2025 እ.ኤ.አ እቅድ ዘጠኝ ወር መጨረሻ ድረስ 31 ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር ጠቅላላ ሀብት በማስመዝገብ የፋይናንስ አቅሙን አረጋግጧል። ከዚህ ውስጥ የኢንቨስትመንት ዕዳው 14 ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር ነው፡፡ የተጣራ ሀብቱ ደግሞ 13 ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር ሲሆን ጠቅላላ ሀብቱ ደግሞ 28 ነጥብ ሶስት ቢሊዮን ብር ደርሰዷል፡፡ ይህ የኢንቨስትመንት ዕዳ ከጠቅላላ ሀብት 50 በመቶ በታች መሆኑ የኮርፖሬቱ የፋይናንስ ሁኔታ ጤናማና ከአበዳሪ ተቋማት ተበድሮ ለመስራት ያለውን አቅም በጥሩ ደረጃ ላይ እንደሚያስቀምጠው ያመላከተ ነው።

የኮርፖሬቱ ሀብት እድገት ተከታታይ ነው። በ2023 እ.አ መጨረሻ ላይ ከነበረው 19 ነጥብ 28 ቢሊዮን ብር ጋር ሲነጻጸር በብር አምስት ነጥብ 92 ቢሊዮን ብልጫ አሳይቷል። ከሪፎርም በኋላ ባሉት ስድስት ዓመታት (እ.ኤ.አ ከ2018 ጀምሮ) በአማካይ በየዓመቱ የሁለት ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር የሀብት ዕድገት አስመዝግቧል።

ይህ የሀብት እድገት ከኮርፖሬቱ የተጣራ ትርፍ እድገት ጋር የተያያዘ ነው። ሪፎርሙ ከተጀመረበት እ.ኤ.አ ከ2018 የ273 ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ብር የተጣራ ትርፍ ወደ አንድ ነጥብ 79 ቢሊዮን ብር በማሳደግ ከስድስት እጥፍ በላይ ብልጫ ያሳየ ነው። ይህ ትርፍ በዋነኛነት የተገኘው በቢዝነስ አመራር መሻሻል፣ በምርት ስራ ቅልጥፍና እና በስትራቴጂ ለውጥ ነው። ከዚህም በተጨማሪ በሪፎርም ወቅት ስድስት ኩባንያዎች የነበረባቸው የ94 ነጥብ አራት ሚሊዮን ብር ኪሳራ በ2024 ዓ.ም ወደ አምስት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ብር እና አንድ ኩባንያ ብቻ ዝቅ ማድረጉ የፋይናንስ ማኔጅመንት መሻሻሉን ያሳያል።

የኮርፖሬቱ ኩባንያዎች አንዱ ከሌላው ጋር የተሳሰሩና ተመጋጋቢ በመሆን ውጤታማ እንዲሆኑ እየተሰራ ነው። ይህ ስትራቴጂ በተለያዩ አገራዊ ችግሮች ውስጥ ሲያልፉ አንዱ የአንዱ ገበያ በመሆን መጓዝ እንዲችሉ አስችሏል። ለአብነትም ዳሽን ቢራ ፋብሪካ ቀደም ሲል ከውጭ ያስገባው የነበረው ካሳ በአሁኑ ጊዜ በባህር ዳር በሚገኘው ግዮን ፕላስቲክ ፋብሪካ እየተመረተ ይቀርብለታል።

ቆርኪም ከውጭ ምንዛሪ ተፈልጎ ከውጭ ይገባ የነበረ ሲሆን፣ አሁን በኮምቦልቻ ከተማ የተቋቋመው ቆርኪ አምራች ፋብሪካ ለዳሽን ብቻ ሳይሆን ለሌሎች የቢራና ለስላሳ ፋብሪካዎችም በማቅረብ የውጭ ምንዛሪ ብክነትን በመቀነስ የክልሉን ኢኮኖሚ እየደገፈ ነው። እንደዚሁም በጎንደር የሚገኘው ብቅል ፋብሪካ የሚያመርተው ብቅል ለዳሽን ቢራ የሚቀርብ በመሆኑ የሁለቱ ኩባንያዎች ትስስር ከፍተኛ ነው። የጨርቃጨርቅ ዘርፍ ግብዓት የሆነው የተዳመጠ ጥጥ ደግሞ ከአህት ኩባንያው ከገንዳ ውሃ የጥጥ መዳመጫ ፋብሪካ ይቀርብለታል። በተጨማሪም፣ ሁለት የትራንስፖርት ድርጅቶች የኩባንያዎችን ምርቶች ከቦታ ቦታ በማመላለስ፣ እንዲሁም ከውጭ የሚገባውን ምርት ወደ ሀገር ውስጥ በማጓጓዝ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያደረጉ ነው። ኩባንያዎቹ ለአካባቢው ማኅበረሰብ ለስድስት ሺህ 494 የስራ ዕድሎችን ከመፍጠራቸው በተጨማሪ ፣ አንዱ ለአንዱ ገበያ በመሆን በክልል ደረጃ ፣ አልፎም በአገር ደረጃ ትልቅ አስተዋፅኦ እያደረጉ ይገኛሉ። ይህ የተቀናጀ አሰራር የኮርፖሬቱን የልማት ተልዕኮ በተግባር ያሳየ ነው።

ንጋት ኮርፖሬት በአማራ ክልል ዘላቂ የኢኮኖሚ መሰረት ለመጣል ያለመው ጥረት በስትራቴጂካዊ ዕቅዶቹ ፣ በተቀናጀ የስራ ፍሰቱ እና በተጨባጭ ያመጣቸው ለውጦች ተጠናክሮ እየተሰራበት ነው ያሉት አቶ ውድነህ ኮርፖሬቱ ከለውጡ በፊት ተዘጋጅቶ ሲተገበር የነበረው የአምስት ዓመት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ በውስጥ አቅም የተዘጋጀ እንጂ በጠንካራ ፍኖተ-ካርታ ላይ ያልተመሰረተ ነበር። ይሁን እንጂ ከ2022 እ.ኤ.አ. ጀምሮ የሚተገበር የ10 ዓመት ፍኖተ-ካርታ እና እ.ኤ.አ ከ2022-2026 የሚቆይ የዓምስት ዓመት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ አዘጋጅቶ በመተግበር ላይ ይገኛል። የአሁኑ የስትራቴጂ ዝግጅት ሂደት አሳታፊ የመፈፀም አቅምንና ነባራዊ ሁኔታን ያገናዘበ ቀጣይነት ያለው



በደብረብርሃን ከተማ አስተዳደር መጠለያ ለሌላቸው ወገኖች የተገነባ መኖሪያ ቤት



በዋግኽምራ ዞን ተላጀ አያሌው አስረስ ከፍተኛ ሁለተኛ ደ/ት/ቤት

እድገትን የሚያረጋግጥ እንዲሆን ታስቦ እየተሰራበት ነው።

የንጋት ኮርፖሬት ቁልፍ ተልዕኮ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ባላቸውና አዋጭ በሆኑ የኢኮኖሚ መስኮች በመሰማራት የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ልማት ማምጣት ነው። ኩባንያዎቹም የአማራ ክልልን ኢንዱስትሪያላይዜሽንና ግብርና ልማት እንዲያግዙ ሆነው በቁርጠኝነት እየተሰራበት ይገኛል። ንጋት ኮርፖሬት ከውስጣዊ የስትራቴጂ ለውጦች ጀምሮ እስከ ተጨባጭ የኢኮኖሚ ልማት ድረስ ባስመዘገባቸው ውጤቶች ለክልሉ ዘላቂና ሁሉን አቀፍ እድገት እያበረከተ ያለው አስተዋፅኦ እጅግ የላቀ ነው።

ንጋት ኮርፖሬት ወደ ህዝብ ከተዘዋወረ በኋላ በአማራ ክልል ህዝብ ህይወት ላይ የፈጠረው ለውጥ በርካታ ነው። ኮርፖሬቱ በፋብሪካዎቹ የማምረት እና የሽያጭ አቅም መሻሻል የጀመረውን ጉዞ የገበያ ትስስር በመፍጠር ለሴቶችና ወጣቶች ሰፊ የስራ ዕድል በማቅረብ ፣ ተጨማሪ ሃብት በማመንጨት እና ከፍተኛ ግብር በመክፈል ቀጥሏል። ከዚህ በተጨማሪ ለእርሻ ምርቶች ሰፊ ገበያ በመሆን ፣ በግብርና ምርቶች ላይ እሴት በመጨመር እና ለገበያ በማቅረብ ለግሉ ዘርፍ ምሳሌ የሚሆኑ በርካታ ኢንዱስትሪዎችን ማፍራት የቻለ ነው፡፡ አሁን ላይ ንጋት ኮርፖሬት እና ኩባንያዎቹ የክልሉን የገበያ ጉድለቶች ለመሙላት ሰፊ ስራ እየሰሩ ነው።

ንጋት የክልሉን ግብርና በማዘመን ለምግብ ዋስትና እና ሥነ-ምግብ ስርዓት መረጋገጥ አስተዋጽኦ እያደረገ ነው። በዚህ ረገድ በተሰራው ስራም ባለፉት ጥቂት አመታት 118 ዘመናዊ ትራክተሮች፣ 150 ማረሻዎች እና 11 ኮምባይነሮች ከ500 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ በማድረግ ለአርሶ አደሮችና ለግብርና ኢንቨስትመንት ማኅበረሰብ አቅርቧል። በተጨማሪም ባለፉት አምስት ዓመታት 28 ሽህ 843 የውሃ መሳቢያ ፓምፖችን በማቅረብ የአርሶ አደሮችን የመስኖ ስርዓት አሻሽሏል። እ.ኤ.አ በ2024/25 ምርት ዘመን ተጨማሪ 13 ትራክተሮች እና 6 ኮምባይን-ሃርቨስተሮች ቀርበዋል፤ እንዲሁም 74 ትራክተሮች እና 10 ኮምባይን-ሃርቨስተሮች በመጓጓዝ ላይ ናቸው። በአጠቃላይ እስከ አሁን ድረስ 33 ሽህ 332 ፓምፖች ለአርሶ አደሩ ቀርበዋል።

የንጋት ህዝባዊነት መገለጫው የሚያገኘውን ማንኛውም ገቢ የህብረተሰቡን ፍላጎት ሊያሟላ በሚችል የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ልማት ላይ ማዋሉ ነው። ንጋት ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ከኢንቨስትመንት ከሚያገኘው ትርፍ እና በኩባንያዎቹ አማካኝነት ለትምህርት ቤት ግንባታ ፣ ለጤና ተቋማት ግንባታ ፣ ለመንገድ ስራ ፣ ለስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ግንባታ ፣ ለቢራ ገብስ አምራች አርሶ አደሮች ድጋፍ ፣ ለአረጋዊያን መጠለያ ቤት ግንባታ ፣ ለንፁህ የመጠጥ ውሃ ግንባታ እና ለኪነ ጥበብ ዘርፉ ከፍተኛ ድጋፍ አድርጓል።

ለአብነትም ለወገን ደራሽ ወገን ነው በሚል በዋግኽምራ ዞን በተለያዩ ጊዜ የተደረገ ድጋፍ ፣ በደብረብርሃን ከተማ አስተዳደር መጠለያ ለሌላቸው ወገኖች በዳሽን ቢራ ፋብሪካ የተገነባው የመኖሪያ ቤት ፣ በወራሪው የህውሃት ጦርነት ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉ ዜጎች የተደረገ ድጋፍ ፣ ወደ ዩኒቨርስቲ በከፍተኛ ውጤት ለገቡ ተማሪወች የተደረገ ስጦታ ፣ ለደብረ-ታቦር ከተማ ዳግማዊ ቴወድሮስ የተደረገ የኮምፒዩተር ድጋፍ እና ቻግኒ አካባቢ ለተፈናቀሉ ወገኖች የተደረገ ድጋፍ ከብዙ በጥቂቱ ለህዝብ ከተደረጉት ድጋፎች መካከል መሆናቸውን አቶ ውድነህ ገልፀውልናል፡፡

በተጨማሪም ለጎርጎራ ገበታ-ለሀገር ፕሮጀክት፣ ለአገር ውስጥ ተፈናቃዮች እና ለህልውና ዘመቻው የተደረገው የ214 ሚሊዮን ብር ድጋፍ ይጠቀሳል። በአጠቃላይ ንጋት እስካሁን ከ700 ሚሊዮን ብር በላይ ድጋፍ አድርጓል። ንጋት ለአማራ ክልል ህዝብ ልማትና እድገት ያበረከተው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ቢሆንም በቀጣይም የህብቱ ባለቤት በሆነው የክልሉ ህዝብ ድጋፍ እና አጋርነት የበለጠ ለመስራት ይተጋል።

ኮርፖሬቱ አሁን ክልሉ ያጋጠመውን ችግር ተቋቁሞ ለህዝብ ደራሽ ለመሆን የቀውስ ጊዜ አመራር ዕቅድ አዘጋጅቶ ተግባራዊ እያደረገ ነው። የፀጥታ ሁኔታ ፣ የውጭ ምንዛሬ እጥረት ፣ የሥራ ማስኬጃ በጀት እጥረት ፣ የጥሬ ዕቃና የማሽነሪ መለዋወጫ አቅርቦት እጥረት ፣ የመብራት መቆራረጥ ፣ የትራንስፖርት መቆራረጥና የዋጋ መናር ፣ እንዲሁም የሰራተኞች የኑሮ ውድነት ተለይተው የመቋቋሚያ ስልቶች (Resilience Strategies) በመዘርጋት ዕቅዱን ለማስፈጸም ርብርብ ተደርጓል። በስራ ሂደት ውስጥ ችግሮች ቢኖሩም ፣ እንደ ባህሪያቸው መሰረት ለመፍታት ጥረት ተደርጓል።

ኮርፖሬቱ እ.ኤ.አ ከ2022 ጀምሮ የ10 ዓመት ፍኖተ-ካርታ እና እ.ኤ.አ ከ2022-2026 የሚቆይ

# ልማት/ኢኮኖሚ

የ5 ዓመት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ በማዘጋጀት የክልሉን የልማት ፍኖተ ካርታ ፍላጎትና ዓላማ ጋር የተጣጣመ እንዲሆን አድርጓል። በ2024 በጀት ዓመት 200 ሚሊዮን ብር ለማህበራዊ ልማትና ኃላፊነት ስራዎች ለመመደብ ታቅዶ፣ 71 ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ብር ለተለያዩ የትምህርት ቤቶች ግንባታ፣ የሕክምና መሳሪያዎች፣ ለተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ እና በድርቅ ለተጎዱ አካባቢዎች የሰብዓዊ ድጋፍ ተደርጓል።

ንጋት ኮርፖሬት ከሌሎች አጋር አካላት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ከመቼውም ጊዜ በላይ ተጠናክሯል። ኩባንያዎቹ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ሙያና ቴክኒክ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎችና መምህራን የስራ ላይ ልምምድ የሚካሄድባቸዉ የጥናትና ምርምር ማእከላት በመሆን እያገለገሉ ሲሆን በየአካባቢያቸውም ማህበራዊ ኃላፊነታቸዉን እየተወጡ ነው።

የፋብሪካዎቹ የማምረትና ሽያጭ አቅም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ሲሆን የገበያ ትስስር በመፍጠር ፣ ለሴቶችና ወጣቶች ሰፊ የስራ እድል በመፍጠር ፣ ተጨማሪ ሃብት በማመንጨትና ከፍተኛ ግብር በመክፈል ለግሉ ዘርፍ በምሳሌነት የሚታዩ በርካታ ኢንዱስትሪዎችን በማበራከት ላይ ይገኛሉ።

በ2023/24 የምርት ዘመን የኤክስፖርት ምርት አቅርቦትን ለማሳደግ ከአርሶ አደሮች እና ባለሀብቶች ጋር በኮንትራት ፋርሚንግ ሰፊ ስራ ተሰርቷል። በተጨማሪም፣ በመንግስት ግዴታን በመወጣት ረገድ በ2023 በጀት ዓመት ስምንት የንጋት ኩባንያዎች በፌደራል ደረጃ የታማኝ ግብር ከፋይነት ሽልማት አግኝተዋል። ዳሽን ቢራ በአገር ደረጃ አራተኛው ትልቁ ግብር ከፋይ እና ልዩ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ እውቅና ተሰጥቶታል።

በመጨረሻም ንጋት ኮርፖሬት የያዘውን እሳቤዎች ዳር ለማድረስ ሁሉም የአጋር አካላት ርብርብ ይሻል ያሉት ኦፊሰሩ በተለይም ደግሞ የክልሉ ህዝብ ኩባንያዎቹን በመጠበቅ እና ምርቶቻቸውን በመግዛት ድጋፉን ማሳየት እንዳለበት አሳስበዋል። የክልሉ መንግስትም አሁን የጀመረውን ድጋፍ አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል። ሌሎች መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም ትብብራቸውን አጠናክረው በመቀጠል በጋራ በመስራት የክልሉንና የአገራችንን ኢኮኖሚ ለማሳደግ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ ጥሪ በማቅረብ ያላቸውን ሃሳብ አስተያየት አጠቃለዋል፡፡

የዝግጅት ክፍሉም አቶ ውድነህ ለሰጡን ማብራሪያና ምላሽ ምስጋናውን አቅርቦ ንጋት ኮርፖሬት የአማራ ህዝብ ሀብት በመሆኑ ከማህበራዊ ልማትና ከህዝብ ተጠቃሚነት አንፃር ትልቅ ሀላፊነት እንዳለበት ያምናል። በአሁኑ ወቅት ስድስት ሺህ 494 ሰዎች የስራ እድል መፍጠሩ የሚደነቅ ቢሆንም የክልሉን ስራ አጥነት ለመቀነስ ተጨማሪ የስራ እድሎችን መፍጠር ይጠበቅበታል። በተለይም ለወጣቶችና ለሴቶች ቅድሚያ በመስጠት የኑሮ ደረጃቸውን ማሻሻል አለበት።

ንጋት የመሰረተ ልማትን በማፋጠን የህዝቡን የኑሮ ጥራት ለማሻሻል ወሳኝ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ማለትም ለትምህርት ቤት ፣ ለጤና ተቋማት ፣ ለመንገድና ለንጹህ የመጠጥ ውሃ የሚያደርገውን ድጋፍ አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም የግብርናውን ዘርፍ በማጠናከር የአፈር ማዳበሪያና የእርሻ መሳሪያዎችን በማቅረብ እንዲሁም በኮንትራት ፋርሚንግ የአርሶ አደሩን ምርታማነት በማሳደግ የክልሉን የምግብ ዋስትና በማረጋገጥና የገበሬውን ኑሮ ማሻሻል ላይ ተግቶ በመስራት ተጨባጭ ለውጥ ማስመዝገብ አስፈላጊ ነው።

ኮርፖሬቱ የህብረተሰብ ክፍሎችን መደገፍ ላይ ትኩረት በማድረግ ለህፃናት ፣ ለአካል ጉዳተኞች ፣ ለአረጋውያንና ለችግረኞች የሚደረገውን ማህበራዊ ድጋፍ ማስፋት ተገቢ ሲሆን በተለይም በክልሉ ባሉ ወቅታዊ ችግሮች (እንደ የፀጥታና የተፈናቃዮች ጉዳይ) የሰብዓዊ ድጋፎችን በማስፋት ለህዝብ ደራሽ የማድረግ ስራውን አጠናክሮ ማስቀጠል ያስፈልጋል፡፡

ንጋት የአማራ ህዝብ ሀብት በመሆኑ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ማጠናከር አለበት። ስራዎቹና ፋይናንሳዊ አፈፃፀሙ ለህዝብ ግልጽ መሆን ሲኖርበት ፣ የክልሉ ምክር ቤት ተጠሪ በመሆኑ ይህንን ተጠያቂነት በተግባር ማረጋገጥና የህዝብን እምነት ማጠናከር ይጠበቅበታል። የህዝቡን የባለቤትነት ስሜት ማሳደግ ሌላው ወሳኝ ጉዳይ ነው። ንጋት የህዝብ ሀብት መሆኑን በማስተዋወቅ የተሻለ ግንዛቤ መፍጠርና ህዝቡ የድርጅቱ ባለቤት መሆኑን በተግባር እንዲሰማው ምርቶቹንና አገልግሎቶቹን እንዲጠቀም በማበረታታት የባለቤትነት ድርሻውን እንዲወጣ መጋበዝ አለበት።በድርጅቱ እቅድ ዝግጅትና አፈፃፀም ላይ የህዝብን ተሳትፎ ማጠናከር አስፈላጊ ነው። ህዝቡ የድርጅቱ አካል መሆኑን በተግባር ሲያይ ለስኬቱ የበለጠ አስተዋፅኦ ያደርጋል።

ንጋት የክልሉን ኢኮኖሚ ማነቃቃት ላይ በማገዝ ህዝቡ የጣለበትን ሀላፊነት እንዲወጣ መስራት አለበት። አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን በመሳብና ነባር ኩባንያዎችን በማጠናከር የክልሉን ኢኮኖሚ ለማሳደግ ግንባር ቀደም ሚና መጫወት ይጠበቅበታል። የክልሉን ህዝብ የኑሮ ደረጃ በማሻሻል፣ የኢኮኖሚ እድገትን በማስፋፋትና ማህበራዊ መሰረተ ልማቶችን በማሟላት ረገድ ከፍተኛ ሚና አለው። ይህንን ሀላፊነት በብቃት ለመወጣት ከህዝቡና ከመንግስት ጋር ያለውን ትስስር አጠናክሮ መስራቱን መቀጠል አለበት።

በአጠቃላይ ንጋት ኮርፖሬት ያለውን አቅም በአግባቡ በመጠቀም ዘመናዊ የንግድ ስትራቴጂዎችን በመተግበር ብሎም የማኅበራዊ ኃላፊነቱን በአግባቡ በመወጣት ለሌሎች አገራዊ የልማት ድርጅቶች አርዓያ መሆኑን በተግባር ማሳየት ከኮርፖሬቱ በእጅጉ የሚጠበቁ አንኳር ጉዳዮች ናቸው፡፡ እየተሰሩ ያሉ ስራዎችን የተለያዩ የሚዲያ አማራጮችን ተጠቅሞ የሕዝብን ሀብት ሕዝቡ እንዲጠብቀውና እንዲያሳድገው በሚገባው ልክ ለሕዝብ ተደራሽ ማድረግ ፣ የሚሰሩ ስራዎች ለህዝብ ግልፅ ማድረግ ፣ ተጠያቂነት የሰፈነበት አሰራሮችን በተጨባጭ ማሳየት ፣ አዳዲስና ቀጣናዊ ችግሮችን የሚፈቱ የፈጠራ ውጤቶችን በማምጣት የኢንዱስትሪውን ዕድገት ማፋጠን ፣ የአካባቢ ጥበቃን እና ማኅበራዊ ፍትህን ያማከለ የንግድ ሥራዎችን ማስፋፋት ፣ በሁሉም የሥራ ዘርፎች ዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ቅልጥፍናንና ምርታማነትን ማሳደግ እና ውስብስብ የልማት ፕሮጀክቶችን በጋራ ለመተግበር የጋራ አጋርነቶችን መፍጠር ይኖርበታል እንላለን ሰላም።

# ጎብኝና መዳረሻው

በህያው ተስፋዬ

የቱሪዝም አመጣጥን በተመለከተ ዓለም አቀፍ ጥናቶች እንዲህ ይላሉ፡፡ የቱሪዝምን አነሳስ በትክክል ይህ ነው ብሎ ለማስቀመጥ ቢከብድም በጥንት ዘመን ሰዎች በተፈጥሮ የድርቅ ወይም የርሀብ አደጋ ሲገጥማቸው ምግብ ፍለጋ መንቀሳቀሳቸው፣ በጦርነት ወቅት ደግሞ ሞትን ሽሽት ወይም ደህንነታቸውን ለማስጠበቅ ወደ ሰላማዊ አካባቢዎች ያደርጉት የነበረው ጉዞ እና በጊዜ ሂደት ደግሞ እንደ ጊዜ ማሳለፊያነት ይወስዷቸው የነበሩ ከቦታ ቦታ እንቅስቃሴዎች መነሻ ሊሆኑ እንደሚችሉ ግምታቸውን ያስቀምጣሉ፡፡ ነገር ግን ደስታን ለማግኘት ተብሎ ቱሪዝም እንዳልተጀመረ እነዚሁ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡

የዘመናዊው ቱሪዝም መነሻ ደግሞ በተለይ በ17ኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ የተለያዩ የአውሮፓ ሀገራት ወጣቶች በቡድን በመሆን የተለያዩ ሀገራትን ታሪክ፣ ባህልና ኪነ- ጥበብ የማየት እንቅስቃሴያቸው እንደሆነ ይነገራል፡፡

ይሁን እንጂ በርካታ ዘመናትን ወደኋላ ተጉዞ የተለያዩ የመነሻ ምክንያቶችን የሚያጣቅሰው ቱሪዝም ዛሬ ላይ ከመዝናኛነቱ በላይ ለበርካታ ሀገራት ዋነኛ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ሞተር፣ በዓለም ላይ በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ሰዎች የስራ ዕድል ምክንያት እና ከዚሁ ከቱሪዝም የሚገኘው ገቢ ደግሞ የተፈጥሮና ባህላዊ ቅርሶችን በመጠበቅ መጭው ትውልድ እነዚህን ሀብቶች እንዲጠቀምባቸው ከፍተኛ ሚና የሚጫወት ኢንዱስትሪ ሆኗል፡፡ እግረ መንገዱንም በዓለም ህዝቦች መካከል የሚፈጥረው የባህል ፣ ቋንቋና የአኗኗር ዘይቤዎች ልውውጥ ያለው ዕድልም ቀላል አይደለም፡፡

በርካታ የጥናት የጽሁፎች እንደሚያሳዩት በዓለም ላይ ካሉ ሀገራት ሁሉ ሰዎች ለጉብኝት ከቦታ ቦታ ይንቀሳቀሳሉ፡፡ በዚህም መሰረት በዓለም አቀፍ ደረጃ ፈረንሳይ በየዓመቱ ወደ 90 ሚሊዮን የሚጠጉ ዜጎቿ ለጉብኝት ወደ ተለያዩ የዓለም ሀገራት በመንቀሳቀስ ቀዳሚ ስትሆን፣ በ83 ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ስፔን፣ በ79 ነጥብ ሦስት አሜሪካ፣ በ65 ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ቻይና እና በ64 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ደግሞ ጣልያን በተከታታይነት ይጠቀሳሉ፡፡ እ.ኤ.አ በ2024 ዓ.ም በጥቅሉ በዓለም ላይ 1.45 ቢሊዮን የሚገመቱ ቱሪስቶች በዓለም ላይ ተንቀሳቅሰዋል፡፡

ይህን ያህል ቁጥር ያለው ቱሪስት ከሚንቀሳቀስባቸው መስህብ ቦታዎች ወይም የቱሪስት መዳረሻዎች መካከል በከተማ ደረጃ የእንግሊዟ ለንደን ከተማ፣ የተባበሩት አረብ ኤሚሬቷ ዱባይ፣ ሲንጋፖር፣ የማሌዢዋ ካላላምፑር፣ የአሜሪካዋ ኒዮርክ እና የፈረንሳይ ዋና ከተማ ፓሪስ እያሉ በቅደም ተከተል ይቀጥላሉ፡፡

እንዲሁም የጎብኝዎችን ቀልብ ከሚስቡና በብዛት የሚጎበኙ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ቅርሶችና ቦታዎች ወይም መዳረሻዎችንም በተመለከተ የፈረንሳዩ ኤፈል ታዎርና የኪነ ጥበብ ሙዚየሟ ሉውቨር ሙዚየም፣ ሮም ከተማ የሚገኘው አምፊ ቴአትር ማሳያ የነበረው ኮሎሰም፣ አሜሪካ የሚገኘው ታላቁ ጭሳማ ተራራ፣ የህንዱ ታጅ ማህል ሲሆኑ በአፍሪካ ደረጃ ደግሞ የታንዛንያው ኪሊ ማንጀሮ ተራራ፣ የኬንያው ማሳይ ማራ ብሔራዊ ፓርክ፣ የደቡብ አፍሪካው ጠረጴዛማው ተራራ፣ የዝምባቡዌ ቪክቶሪያ ፏፏቴ፣ የግብጽ ፒራሚዶች፣ መዲና ማራካሽ፣ የሀገራችን የሰሜንና የባሌ ብሔራዊ ፓርኮች፣ የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያን፣ የንጉስ አፄ ፋሲል ቤተ መንግስት፣ የአክሱም ሀውልት፣ የአዋሽና የኦሞ ሸለቆዎች ይጠቀሳሉ፡፡

በቱሪዝም ዙሪያ ዓለም አቀፍ ሁኔታውን ለማሳያነት ያክል ይህን ካልን የአማራ ክልልን አስመልክቶ የቱሪዝም እንቅስቃሴው በተለይም ደግሞ በመዳረሻዎቹ ዙሪያ ያለውን ወቅታዊ መረጃ በተመለከተ ዘርዘር አድርገን ልናስነብባችሁ ወደናል፡፡ ለዚህም ደግሞ የክልሉ ባህልና ተሪዝም ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ አባይ መንግስቴ የሰጡንን መረጃ እንዲህ አሰናድተንላችኋል ና መልካም ንባብ፡፡

ቱሪዝም የሰዎችን እንቅስቃሴ የሚያሳይ ነው፡፡ ቱሪስት ወይም ጎብኝ ማለት ደግሞ የአንድን አካባቢ፣ ባህል፣ ታሪክና የመሳሰሉ ጉዳዮችን ለማየት ከመደበኛው የመኖሪያ አካባቢው ወደ ሌላኛው አካባቢ የተንቀሳቀሰ ሰው ማለት ነው፡፡ ይህ ሰው ግን ጎብኝ ለመባል በመዳረሻው ቢያንስ ከ24 ሰዓታት ያላነሰና ከአንድ ዓመት ያልበለጠ ቆይታ ሊኖረው ይገባል፡፡

የቱሪስት መዳረሻ ማለት ደግሞ ቱሪስቱ ወይም ጎብኝው ሊያየው ወይም ሊያውቀው ፈልጎ የሚመጣባቸው ሁሉ መዳረሻዎች ይባላሉ፡፡ ያ ማለት ደግሞ ሀገር ሊሆን ይችላል፣ ኃይማኖታዊ ቦታዎችና ስርአቶች ሊሆን ይችላል፣ የተፈጥሮ ፀጋዎችን ሊሆን ይችላል ወይም ደግሞ ሁሉንም ሊሆን ይችላል ማለት ነው፡፡

ይህን መዳረሻ ደግሞ ለጎብኝዎች ምቹ ለማድረግ የመንገድ፣ የመብራት፣ ውሃ፣ መዝናኛ፣ ሆቴልን ጨምሮ የማረፊያ ቦታዎችና የመሳሰሉት ሥራዎች ደግሞ የቱሪዝም መዳረሻ ልማት ይባላል፡፡

ከዚህ አኳያ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እጅግ ሰፊ የሚባል ተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊ፣ ባህላዊና ኃይማኖታዊ የቱሪስት መዳረሻዎች አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል ደግሞ የተወሰኑት በሀገርና በአህጉር ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያላቸው የቱሪስት መዳረሻዎች ይገኛሉ፡፡ እነዚህም ፡-

1ኛ- ባህር ዳርና የጣና ዙሪያ ሲሆን፡- ይህ ጢስ ዓባይ ፏፏቴን፣ ዘጌና የጣና ደሴቶችና ሌሎች የአካባቢውን የተፈጥሮ ፀጋዎች ያካተተ ነው፡፡

2ኛ- ጎንደርና አካባቢው፡- በዚህ ውስጥ የሚካተቱት ደግሞ ራሱ ጎንደር ከተማ፣ ጎርጎራናጣና ዙሪያው፣ ገዳማት፣ የአፄ ፋሲል ቤተ-መንግስት እና ሌሎች የአካባቢው የተፈጥሮ



አቶ ዓባይ መንግስቴ

የአማራ ክልል ባህልና ቱሪዝም ምክትል ቢሮ ኃላፊ

ፀጋዎችን ያጠቃልላል::

3ኛ- የሰሜን ብሔራዊ ፓርክ፡- ይህ ፓርክ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የሀገራችን ብቸኛው የተፈጥሮ ቅርስ ሆና በዩኔስኮ የተመዘገበ መዳረሻ ነበር:: አሁን ላይ ደግሞ የባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ ዓለም አቀፍ የቱሪስት መዳረሻ ሆኖ ተቀላቅሎታል:: በሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ ራሱ የተፈጥሮ መልክአ ምድሩ፤ በተለይ ደግሞ የሀገሪቱ ረጅሙ የራስ ዳሽን ተራራ፣ ዋልያ፣ ቀይ ቀበሮ፣ ጭላዳ ዝንጀሮ፣ልዩ ልዩ አዕዋፋት እና እጽዋትን የመሳሰሉ ብርቅየ የተፈጥሮ ፀጋዎች ያሉት አካባቢ ነው::

4ኛ- የቅዱስ ላሊበላና ዙሪያው፡- በዚህ መዳረሻ ራሱ ቅዱስ ላሊበላና ሌሎች ውቅር አብያተ ክርስትያናትን ጨምሮ ሌሎች የወሎ አካባቢ የተፈጥሮ ፀጋዎችን የሚያካትት ነው::

እነዚህ የቱሪስት መዳረሻዎች በዋናነት የሀገር አቀፍም ሆነ የዓለም አቀፍ ቱሪስት መዳረሻች በመሆን ለዘመናት አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ ናቸው:: ቢሆንም ግን በክልሉ ላይ ከእነዚህ በተጨማሪ ከ37 ያላነሱ የቱሪስት መዳረሻዎች ይገኛሉ:: ለምሳሌ የደሴ ከተማ አይጠየፍና "የ" ምሮ " ቤተ መንግስት እንዲሁም በዙሪያው ያሉ የሎጎ ሀይቅ፣ የውጫሌ ስምምነት የተካሔደበት ቦታ፣ መቅደላ፣ የአድዋ ድል ታሪክ አካል የሆነው የወረኢሉ አካባቢ፣ ኬሚሴ ላይ ደግሞ የሾንኬ መንደር፣ ፍል ውሀዎች፣ ጥንታዊ አብያተ ክርስቲያናት፣ እና መስጂዶች አሉ:: ደብረ ብርሃንን ማዕከል ያደረጉ ደግሞ የአፄ ዘረያቆብ ቤተ- መንግስት፣ ደብረ ብርሃን ስላሴ ቤተ-ክርስቲያን፣ አንኮበር ላይ ያለው የአፄ ምኒሊክ ቤተ - መንግስት እና የመሳሰሉ በርካታ መዳረሻዎች አሉ::

አዊ ዞን የዘንገናን ሀይቅ ጨምሮ ሌሎች የተፈጥሮ ፀጋዎች፣ ደብረ ማርቆስ ላይ የንጉስ ተክለ ሀይማኖት ቤተ- መንግስት እና በዙሪያው በርካታ አብያተ ክርስቲያናትና ቤተ- መንግስቶች አሉ:: በተጨማሪም ክልሉ ላይ ከሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ ሌላ በተለያዩ አካባቢዎች ስምንት የሚሆኑ ፓርኮች እንዲሁም ብርቅየ አዕዋፋት፣ አራዊት እና እጽዋት የሚገኙበት ለአየር ንብረት መስተካከል አስተዋጽኦ የሚያደርጉ፣ የከርሰ ምድርና ገፀ ምድር ውሃ መበልጸግ አስተዋጽኦ ያላቸው የቱሪስት መዳረሻ የሚሆኑ ሰባት ያክል ጥብቅ የማህበረሰብ ደኖች ይገኛሉ::

በተለይ ደግሞ በማይዳሰሱ የቱሪስት መስህብ ዘርፎች የጥምቀትና የመስቀል በዓል አከባበር፣ የአገው ፈረሰኞች በዓል፣ እንግጫ ነቀላ፣አሸንድየና ሶለልን የመሳሰሉ ኃይማኖታዊና ባህላዊ በዓላት እንደየ መከበሪያ አካባቢያቸው ራሳቸውን ችለው ሌላኛው የቱሪስት መዳረሻዎች ናቸው::

ይሁን እንጂ የቱሪስት መዳረሻ ልማት ከእድሳትና ግንባታ ባሻገር በመሰረተ ልማት ግንባታ ብቻ እንኳን ለምሳሌ ከአውሮፕላን ማረፊያ ጀምሮ የአስፓልት መንገድ፣ የውሃ፣ መብራት፣ የስልክ እና ሌሎች የግብአቶች አቅርቦት ከፍተኛ ዕውቀት ያለው የሰው ኃይልና ሀብት የሚጠይቁ በመሆናቸው ቀላል የማይባል ፈተና መሆኑ ግልጽ ነው:: ቢሆንም እንደ ሀገርም ሆነ እንደ አማራ ክልል በጥንካሬ የሚወሰዱ በርካታ ስራዎች ግን ተካሂደዋል::

ለማሳያነት ያክል የቱሪስት መዳረሻዎችን ከገቢ ምንጭነት ባሻገር ለትውልድ እንዲተላለፉ ለማስቻል ያሉበትን ቁመና ከመለየት ጀምሮ በማልማት፣ በመጠበቅና በማሳደግ በኩል ራሱን የቻለ ኃላፊነትና ተጠያቂነት ያለው ተቋም እንዲኖር መደረጉ በራሱ ትልቅ ስኬት ነው:: ምክንያቱም ባለፉት በርካታ ዓመታት የዘርፉን ትልቅነትና ጠቀሜታውን ያለገናዘበ የተቋም አደረጃጀት በመፍጠር የቱሪዝም ልማቱ ማደግ በሚገባው ልክ እንዳያድግ እንቅፋት ሆኖ በመቆየቱ ነው::

ከዚህ አንፃር የክልሉ መንግስት አቅም በፈቀደ መጠን በራሱ ከሚያከናውናቸው ልማቶች በተጨማሪ ከፌደራልና ዘርፉን ከሚያግዙ ዓለም አቀፍ ረጂ ተቋማትጋር በትብብር በተለይ በዋና ዋናዎቹ የቱሪስት መዳረሻዎች ላይ ከፍተኛ የልማት ስራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል:: የቅርቡን ብናይ እንኳን ከረምት በገባ ቁጥር ሊፈርስ ይችላል በሚል ለዓመታት ለህዝቡና ለመንግስት ስጋት ሆኖ የቆየውን የጎንደር አፄ ፋሲል ቤተ መንግስት በክልሉና በፌደራል መንግስት ትብብር በከፍተኛ ወጭ እድሳት እየተደረገለት መሆኑ ከመፍረስ ስጋት ነፃ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ለትውልድ የመሸጋገር ዕድሉን ከፍ ማድረግ ተችሏል:: እንዲሁም በየትኛውም ዓለም የሌለና ብቸኛ የሆነው፣ በርካታ ጎብኝዎችና ፀሐፍት ያየነውን ጥበብ ለመናገር ቃል ያጥረናል እያሉ የዘገቡለት የቅዱስ ላሊበላ ውቅር ቤተ ክርስቲያን በዕድሜ ብዛት ጥንካሬው የላላበትና ወደ መፍረስ የሚሄድ ምልክቶች እየታዩበት በመምጣቱ የሀገሪቱ



የአፄ ፋሲል ቤተ መንግስት



ጣና ቂርቆስ ገዳም

መንግስት ከውጭ ሀገራት ወዳጅ መንግስታት እና ከዩኔስኮ ጋር በመቀናጀት አሁን ላይ የጥገና ዕድል እንዲያገኝ ተደርጓል፡፡

የክልሉ መንግስት ደግሞ በራሱ አቅም ወደ 41 የሚጠጉ አብያተ ክርስቲያናትና መስጂዶች እንዲሁም በዞኖች የሚገኙ የአብያተ ክርስቲያናትና ቤተ- መንግስታት ሙዚየሞችን በአዲስ የመገንባትና የመጠገን ስራዎችን በዕቅድ ይዞ እየሰራባቸው ይገኛል፡፡ ከእነዚህ መካከል ባህር ዳር ላይ በከፍተኛ ወጭ እየተገነባ ያለው የክልሉ ብሔራዊ ሙዚየም፣ እንዲሁም ባህር ዳርን የኮንፈረንስ ከተማ ለማድረግ ታስበው ከሚሰሩ ስራዎች አንዱ የሆነው ባለ አምስት ኮኮብ ደረጃ ያለው ሆቴልና " ጣና ማሪና " የሚል ስያሜ ያለው ማዕከል እየተገነባ ነው፡፡ በተጨማሪም የሎጎ ሀይቅ መዳረሻ ልማት፣ ስራቸው የተጠናቀቀው የዘጌ የቱሪስት መዳረሻ የእግረኛ መንገዶች እና ደቅ ላይ የወደብ ግንባታው ተጠቃሾች ናቸው፡፡

በግል ዘርፍም ቢሆን በቅርቡ የተሰራው የጎርጎራ ኤኮ ሪዞርት የጎብኝ መዳረሻ ከክልላችን አኳያ ልማቱን አንድ እርምጃ ከፍ ያደረገና ሌሎች ባለሀብቶችም በራስ አቅም ሰርቶ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ ከመሆን ባለፈ ለክልሉና ለሀገራዊው የቱሪዝም ልማት የድርሻቸውን እንዲወጡ ዓይን የገለጠ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡

ከዚህ አኳያ ምንም እንኳን የሰላሙ መደፍረስና የበጀት ችግሩ አሁንም ቢሆን ትልቅ ፈተና ሆኖ ቢቀጥልም መንግስት ግን ለባህልና ቱሪዝም ዘርፉ ቀላል የማይባል ትኩረት ሰጥቶ እየተንቀሳቀሰ ያለበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡

ሌላው ስለ መዳረሻዎች ስናነሳ የቱሪስት ወይም የጎብኝዎች ሁኔታ ሳናነሳ ማለፍ አይቻልም፡፡ እንደሚታወቀው ቱሪዝም ማለት የጎብኝዎችና የመዳረሻዎች መገናኘት ማለት ነው፡፡

ከዚያ ውጭ ግን ቱሪስት የሌለበት መዳረሻ የስራ ዕድልም ሆነ ሀብት የማይፈጥር የክልል ወይም የሀገር ሀብት ብቻ ነው የሚሆነው፡፡

ስለዚህ መዳረሻዎችን ከማልማት ባሻገር የጎብኝዎችን መገኘትና መቆየት ማሳደግ የግድ ይላል፡፡ በዓለም አቀፍ ተሞክሮ የጎብኝን ቁጥር ከፍ ለማድረግ ወሳኝ ከሆኑ ጉዳዮች አንዱ የ " ሰላም " ጉዳይ ነው፡፡ ሰላም በሌለበት የቱሪዝም እንቅስቃሴ መዳከም ብቻ አይደለም ሊቆምም ይችላል፡፡ አጠቃላይ የዓለምን የቱሪዝምን እንቅስቃሴ ወደ ምንም አድርሶት የነበረው የ " ኮቪድ 19 " የቅርብ ጊዜ ምስክር ነው፡፡ አሁን ላይ በኛ ሀገር ደግሞ በተለይ በክልላችን የተፈጠረው የእርስ በርስ ግጭት በቱሪዝም እንቅስቃሴው ላይ ቀላል የማይባል አሉታዊ ተጽዕኖ ፈጥሮ ይገኛል፡፡

በተለይ የውጭ ሀገራት ጎብኝዎች የአካባቢውን ግጭት መሰረት በማድረግ የየሀገራቱ ኢንባሲዎች ዜጎቻቸው ወደ ክልሉ እንዳይመጡ ክልከላ ያደርጋሉ፣ በሌላ በኩል ክልሉ እንዳይለማ የሚፈልግ ኃይልም በመኖሩ ወደ ሀገሪቱ የሚመጡ ጎብኝዎች ወደ አማራ ክልል እዳይመጡ የሚከለክለውም ቁጥሩ ቀላል አይደለም፡፡ ቢሆንም ግን ምንም እንኳን ችግሮች ቢኖርም በችግርም ውስጥ ሆኖ ስራ መስራት ስለሚቻል የክልሉ ቱሪዝም ቢሮም ሰላም ከሌለ ቱሪዝም የለም ብለን እጃችንን አጣጥፈን አልተቀመጥንም፡፡ ምክንያቱም እንደ ጤና፣ ግብርና፣ ትምህርት እና የመሳሰሉት አገልግሎቶች የክልሉ ሰላም ፈተና ውስጥ ቢሆንም ለችግሩ እጃቸውን ባለመስጠት እየተንቀሳቀሱ እንዳሉት ሁሉ የቱሪዝም ስራውንም በዚህ መንፈስ በመቃኘት የተፈለገውን ያክል ቱሪስቶች ማምጣት ባንችል እንኳን የተወሰነ ቁጥር የምናመጣበትን ዕቅድ አቅደን ተንቀሳቅሰናል፡፡ በዚህም መሰረት የሀገር ውስጥ ጎብኝን በተመለከተ ምንም እንኳን በፀጥታው ችግር ምክንያት ወደ ክልሉ የመምጣት ስጋት ቢኖርባቸውም አብዛኞቹ ኃይማኖታዊ ጎብኝ በመሆናቸው የቱንም ያክል ፈተና ቢበዛ በዕምነታቸው ምክንያት ችግሩን ጥሰው ይመጣሉ በሚል እሳቤ ባደረግነው እንቅስቃሴ የ2017 በጀት አመቱን የዘጠኝ ወር መረጃ ብቻ ወስደን ብንመለከት ስምንት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ዜጎች ክልሉን መጎብኘት ችለዋል፡፡

የውጭ ሀገራት ጎብኝዎችን በተመለከተም በዓመቱ 25 ሺህ ጎብኝዎች ወደ ክልሉ እንዲመጡ አቅደን ባደረግነው እንቅስቃሴ በዘጠኝ ወሩ ብቻ 16 ሺህ



**የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ**

**ዋልያ**

149 ጎብኝዎች ወደ ክልሉ መምጣት ችለዋል፡፡ ከእነዚህ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገራት ጎብኝዎች በጠቅላላው አምስት ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር በላይ ማግኘት ተችሏል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም 23 ሺህ 500 ለሚሆኑ የክልሉ ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የስራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡

የቱሪዝም ስራውን ሰራን ማለት አንድም ያሉንን የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ሀብቶቻችንን መጠበቅ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በትውልድ ቅብብሎሽ ያገኘነውን ታሪካዊ የጥበብ አሻራ ለቀጣዩ ትውልድ የማሻገር የዜግነት ኃላፊነታችንን ተወጣን ማለት ነው፡፡

በመሆኑም በየደረጃው ያለ የመንግስት መዋቅር ለቱሪስት መዳረሻዎች ትኩረት በመስጠት ዘርፉን ለአሁኑ ዘመን ትውልድ የስራ ዕድል በመፍጠርና እንደ ክልልም የገቢ ምንጭ በማድረግ ለሀገራዊውም ሆነ ለክልላዊ ዕድገቱ በመጠቀም ትልቅ የድህነት መውጫ አማራጭ መንገድ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በህዝቡም በኩል እንዲሁ በተለይ በሚንቀሳቀሱ ቅርሶች ላይ የሚካሔድን ስርቆት በመከላከል በኩል ትልቅ ድርሻ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ምክንያቱም ስለ ቱሪዝም ፀጋዎቻችን ስናነሳ ስለ ባህላችን፣ ጥበባችን፣ ኃይማኖታችን ወይም በአጠቃላይ ስለ ማንነታችን እውቅና እየፈጠርን ነውና ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣ አደራ እላለሁ ብለዋል፡፡

የዝግጅት ክፍሉም በአማራ ክልል እየተካሔደ ያለው የቱሪዝም እንቅስቃሴ ወኔ ያለበት ድፍረት የተሞላ እና ኃላፊነትን ለመወጣት ብዙ ርቀት የተኬደበት እንቅስቃሴ እንደሆነ ለመገምገም ችለናል፡፡ ይህም ስራ ለበርካታ መንግስታዊ ተቋማት ተነሳሽነትን የሚፈጥር ለመሆኑ ጥርጥር የለውም፡፡ በተለይ የክልሉን የፀጥታ ችግር ያገናዘበ ዕቅድ አቅዶ በመንቀሳቀስና ውጤታማ ለመሆን የተደረገው ጥረት ምስጋና የሚገባው ነው ማለት ይቻላል፡፡ ሆኖም ግን ክልሉ ካለው ተፈጥሯዊና ኃይማኖታዊ የቱሪዝም ፀጋዎች አንፃር ከዚህ በላይ ማደግ የሚችልበት አጋጣሚ በመኖሩ በባለ ሀብቱ በኩል ያለው የጋራ ተጠቃሚነት ከፍ ማለት አለበት፡፡ በህዝቡ በኩልም እንዲሁ የሚዳሰሱም ይሁን የማይዳሰሱ የቱሪዝም ሀብቶችን በመጠበቅ በኩል አበርክቶው ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል ፡፡

ምክንያቱም ቱሪዝም ማህበራዊን፣ የባህል መስተጋብርን፣ የትምህርት እና የመማር እድሎችን እና የኑሮ ደረጃን በማሻሻል፣ አወንታዊ ማህበራዊ ተፅእኖዎች በመፍጠር እንዲሁም ማህበራዊ ስምምነትን ሊያሳድጉ የሚችሉት ተፅእኖዎችን በመፍጠር ትልቅ ድርሻ ይጫወታልና ነው፡፡

በአጠቃላይ የቱሪዝም ልማት ቀላል ከማይባለው የገቢ ምንጭነቱ ባሻገር ለበርካታ ዜጎች የስራ ዕድል ምንጭ በመሆኑና ባህላዊ ልውውጥ እና ቅርስ ጥበቃ ያሉ ማህበራዊ እና ባህላዊ ጥቅሞችን ጨምሮ የተፈጥሮ አካባቢን እና ባህላዊ ንብረቶችን እና ወጎችን ለመጠበቅ፣ ድህነትን እና እኩልነትን ለመቀነስ ከማስቻሉ በላይ የመሠረተ ልማት ዝርጋታዎችንም የሚያንቀሳቅስ እና ለነዋሪዎች ከፍተኛ የኑሮ ደረጃን ጭምር ማሻሻል የሚችል ዘርፍ ነው፡፡

ከሁሉም በላይ ደግሞ ቱሪዝም የሀገር ሀብት ለትውልድ ተሸጋሪ እንዲሆን ካለው ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታው አንፃር ጥቅሙን ማጣጣም እንዲቻል የሁሉም ርብርብ እንዲታከልበት አስተያየታችንን በመስጠት ጽሁፋችንን አበቃን፡፡ ሰላም ፡፡

# የሰዓታት የሞት ድግስ

በደፋሩ እምሬ

“ለጤና ውድ ዋጋ የሰጠሁት በአደገኛ በሽታ ተጠቅቸ ለብዙ አመታት የአልጋ ቁራኛ ሆኘ በቆየሁበት ጊዜ ነበር። ያኔ በሽታ የሚባል ርካሽ ነገር ጤናዬን ነጥቆኝ ልሞት እያጣጣርኩ መሆኑን ስረዳ በጣም ተናደድኩ።” ሲል የተናገረው አሁን ላይ በህይወት የሌለ ታዋቂ የቴክኖሎጅ ፈጣሪና በዘመኑ አጠራር “ቢሊኒዬር” በሚባለው የአለም ቱጃሮች ጎራ የሚመደብ ሰው ነው። አንድ ታዋቂ ኢትዮጵያዊ ድምጻዊም “ያለ ጤና ሁሉ ነገር ከንቱ ሁሉ ነገር መና” እንደሆነ በዜማው ተናግሮ አልፏል። ትክክል ነው፤በሽታ ከሰዎች ላይ እንደ ጤና ያሉ ውድ ነገሮችን ከመንጠቅ ጀምሮ ለህልፈት ይዳርጋል። ይህን እውነታ በሚያጠናክር መልኩ “በሽታ የአንድን ሰው የአካል ክፍሎች በማዳከም ህመም እንዲሰማው በማድረግ ተግባራዊ ወይም መደበኛ እንቅስቃሴውን የሚገታ አለፍ ሲልም ለሞት የሚዳርግ ነው” በማለት የገለጹት በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የበሽታዎችና የጤና ሁኔታዎች ምላሽ አሰጣጥ ባለሙያ የሆኑት ሲስተር ሰፊ ደርብ ናቸው። ሲስተሯ ይህን የተናገሩት በኮሌራ አሁናዊ ሁኔታ፣መተላለፊያ መንገዶች፣ዘለቄታዊ መፍትሄ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ በሰጡን ጥልቅና ሰፊ መግለጫ ላይ ሲሆን እኛም ለዚህ አምድ በሚመች መልኩ ሙሉውን መረጃ እንደሚከተለው አቅርበነዋል—መልካም ንባብ።

ኮሌራ ተላላፊ በሚባለው የበሽታ ምድብ ውስጥ የሚካተትና በቀላሉ ከሰው ወደ ሰው ብቻ የሚተላለፍ፣በሰውነት ውስጥ ያለውን ፈሳሽና ጠቃሚ ንጥረ ነገሮችን አጣዳፊ በሆነ ትውከትና ተቅማጥ አሟጦ በማስወጣት አቅም የሚያሳጣ ፈጥነው ካልታከሙት ደግሞ በሰዓታት ውስጥ ለሞት የሚዳርግ ገዳይ በሽታ ነው፤ በማለት ምንነቱን ገልጸዋል።

“ቪብሪዮ ኮሌራ” የሚባል መርዛማ ባክቴሪያ ለኮሌራ መነሻ መንስኤ ተደርጎ የሚወሰድ ሲሆን በዚሁ ባክቴሪያ የተበከለ ምግብና ውሃ ወደ አፋችን ሲገባ፣ ከኮሌራ ታማሚዎች እና በኮሌራ ከሞተ ሰው ጋር ጥንቃቄ የጎደለው ንክኪ ማድረግ የበሽታው መተላለፊያ መንገዶች ናቸው፡፡ ከእንስሳት ጋር በሚደረግ ንክኪ ግን ኮሌራ አይተላለፍም፡፡ ከእኛ ማህበረሰብ አኗኗር አንፃር በተለይ የገጠሩ ህዝብ ከእንስሳት ጋር ሰፊ ንክኪ ስለሚያደርግ በዚህ መንገድ የሚተላለፉ ቢሆን ኑሮ እልቂቱ እጅግ አሳዛኝና አሰቃቂ ይሆን እንደነበር ጨምረው በመጠቆም የበሽታውን መንስኤ አብራርተዋል።

ኮሌራ ከላይ በተገለጸው መልኩ የሚመጣ መሆኑ ከታወቀ በበሽታው ተይዞ ከመሰቃየት አለፍ ሲልም ለሞት ከመዳረግ በፊት ቀድሞ መጠንቀቅ ተገቢ ይሆናል፡፡ ጥንቃቄው ደግሞ ቁልፍ መከላከያ መንገዶች ተብለው የተለዩትን በአግባቡ መተግበር እንደሚገባ የሚያስገድድ ነው፡፡ በመሆኑም ምግብን በሚገባ ማብሰልና ሳይቀዘቅዝ መመገብ፣ አትክልትና ፍራፍሬዎችን ንፅህናቸው በተጠበቀ ወይም በታከመ ውሃ አጥቦ ወዲያውኑ መመገብ፣ሁል ጊዜ ውሃን አፍልቶ እና አቀዝቅዞ መጠጣት ወይም በማከሚያ ኬሚካል አክሞ መጠቀም እና የምግብ እቃዎችን በንጹህ ወይም በኬሚካል በታከመ ውሃ ማጠብ እና መጠቀም የሚሉት ከአመጋገብ ንጽህና ጋር የሚያያዙ መከላከያ መንገዶች ናቸው። መፀዳጃ ቤትን መገንባትና ንጽህናውን በጠበቀ አግባብ መጠቀም፣ ማንኛውንም ከቤት የሚወጣ ደረቅ ወይም ፈሳሽ ቆሻሻን ውሃንና አካባቢን እንዳይበክል በአግባቡ በተመደበለት ስፍራ ማስወገድ፣በኮሌራ በሽታ የታመመን ሰው ልብስ በፈላ ውሃ መቀቀል ወይም በበረኪናና በልብስ ማጽጃ ሳሙና ዘፍዝፎ ማጠብ፣በተቅማጥና ትውከት የተነካካ እቃን፣ወለልና መሬትን ከማጽዳት በፊት በረኪና በማፍሰስ ብክለትን ማስወገድ እና እጅን በወሳኝ ጊዜያት በሳሙና እና በንፁህ ውሃ ሳሙና ከሌለ በአመድ በሚገባ መታጠብ የሚሉት ደግሞ ከአካባቢና ከግል ንጽህና ጋር የሚያያዙ መከላከያ ዘዴዎች ናቸው፡፡ እጅን በወሳኝ ጊዜያት መታጠብ የሚለው የበሽታው መከላከያ ዘዴ ላይ “ወሳኝ ጊዜያት” የተባሉት ምግብ ከማዘጋጀት፣ ከማቅረብ እና ከመመገብ በፊት፣ ከመጸዳጃ ቤት መልስ፣ሕጻናትን ካጸዳዱ በኃላ እና ሕጻናትን ጡት ከማጥባት በፊት እጅን መታጠብ ይገባል። ሌሎች ተጨማሪ ወሳኝ ጊዜያት ብለው የዘረዘሯቸው ደግሞ በበሽታው የሞቱ ሰዎችን አስከሬን በድንገት ከነኩ እና በበሽታው ለተያዙ ሰዎች እንክብካቤ ካደረጉ በኃላ የሚሉት ናቸው። በተለይ በኮሌራ በሽታ ህይወቱ ያለፈ ሰው ከግንዛቱ እስከ ግብዓተ መሬቱ ድረስ ያለው ስነ ስርዓት በጤና ባለሙያዎች በጥንቃቄ እንዲከናወን በማድረግ በአጭር ሰዓታት ውስጥ በመፈጸም መከላከል እንደሚገባ መክረዋል።

ሰዎች በኮሌራ በሽታ ሲያዙ ምልክት ተደርገው የሚወሰዱትን እንዲገልጹልን ጠይቀናቸው ሲመልሱ፡- “የበሽታዉ ዋና ዋና ምልክቶች በድንገት የሚከሰት መጠኑ የበዛ የሩዝ ውሃ የመሰለ ፈሳሽ ፣ አጣዳፊ ተቅማጥና ትውከት ሲሆኑ ብዙ ፈሳሽና ንጥረ ነገር ከሰውነታችን መውጣት ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ እንደ የአፍ መድረቅ፣የአይን መሰርጎድ፣የሽንት መጠን መቀነስ፣የቆዳ መሸብሸብና ድካም እንዲሁም ጠቃሚ የሆኑ የመገጣጠሚያ ንጥር ነገሮች ስለሚወጡ የመገጣጠሚያ ህመም ማስከተል የሚሉት ደግሞ ሌሎች ተጨማሪ ምልክቶች መሆናቸውንም” ዘርዝረው አስረድተዋል።

ከላይ የተጠቀሱት የበሽታው ምልክቶች በሰዎች ላይ ሲታዩ በአስቸኳይ መወሰድ ያለበት እርምጃ ህክምና እንዲያገኙ ማድረግ ነው ካሉ በኋላ የሚሰጠው ህክምናም ሁለት መልክ እንደሚኖረው ተናግረዋል። የመጀመሪያው የህክምና መስጫ ተቋሙ በጣም ሩቅ ከሆነ ታማሚውን ለህክምና እስኪደርስ በህይወት ለማቆየት በቤት ውስጥ በሚደረግ ህክምና ከመሞት መከላከል ይቻላል፡፡ ይኸውም ንጽህናው የተጠበቀ በቤት ውስጥ የሚገኝ ፈሳሽ እየሰጡ ማቆየት ያስፈልጋል፡፡



“ኮሌራ የክልላችን የጤና ስጋት ሆኖ መቀጠል ስለሌለበት ዘለቄታዊ መፍትሄ ማበጀት ላይ መረባረብ ይኖርብናል”

ሲስተር ሰፊ ደርብ

‘ኦ.አር.ኤስ’ የሚባለው በቤት ውስጥ ካለ አንዱን እሽግ በአንድ ሊትር ውሃ በጥብጦ ታማሚውን ባስቀመጠው ወይም ባስታወከው ቁጥር እያጠጡ መሄድ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ከሌለ ደግሞ ስድስት የሻይ ማንኪያ ስኳርንና ግማሽ የሻይ ማንኪያ ጨውን በአንድ ሊትር ንፁህ ውሃ በጥብጦ ታማሚውን ባስቀመጠውና ባስታወከው ቁጥር እየጠጣ ህክምና ቦታ እስኪደርስ ድረስ መርዳት ይገባል፡፡ እነዚህ የመጀመሪያ ደረጃ ህክምናዎች የሚደረጉት በሽታው ራስን በማሳት በሰዓታት ውስጥ የሚገድል ስለሆነ ህክምና መስጫ ቦታዎች ሩቅ በሆኑባቸው የገጠር አካባቢዎች የኮሌራ ተጠቂዎችን ሳይሞቱ ለህክምና እንዲደርሱ ለማገዝ ነው። እድለኛ ሆነው በዚህ መልኩ ህክምና ቦታዎች ላይ ከደረሱ ለበሽታው የሚሰጠው ህክምና በምርመራ የሚጀምር ሲሆን የኮሌራ ባክቴሪያ መኖሩን ለማወቅ የሰገራ ናሙና ትንተና ይደረጋል። ከዚህ ምርመራ በሚገኝ ውጤት መሰረት በሁለት መልኩ ሊታከሙ ይችላል። የመጀመሪያው ብዙውን ጊዜ በአፍ የሚሰጥ በኦ.አር.ኤስ ከታማሚው የወጡ ፈሳሾችን እና ጠቃሚ ንጥረ ነገሮችን እንዲተኩ በማድረግ ህክምና ይደረግላቸዋል። ሁለተኛው ደግሞ ከፍተኛ የሰውነት መሟሸሽ ላለባቸው ታማሚዎች በደም ስር የሚሰጥ ፈሳሽና ጸረ ተዋህስያን መድሃኒቶችን በማዘዝ ህክምና ይደረግላቸዋል። እነዚህ ሁለት እርምጃዎች በሽታው ከተከሰተ በኋላ የሚወሰዱ መቆጣጠሪያ መንገዶች እንደሆኑም ጠቁመዋል። የኮሌራ በሽታ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች የሚያጠቃ ነው፡፡ የቆዩ በሽታዎች ያለባቸው ሰዎች በኮሌራ የሚያዙ ከሆነ ሰውነታቸው በሽታውን የመከላከል አቅሙ የተዳከመ ስለሚሆን ቶሎ የመጠቃት እድላቸው ይሰፋል፤ የሚያመጣው የሞት መጠንም ሊጨምር ይችላል፡፡ በዚህ መልኩ ጤናን በማወክ የሚጀምረው ኮሌራ ሰዎች ወጥተው ወርደው መስራት ስለማይችሉ ምጣኔ ሀብታቸው ይቀንስና ለርሃብ፣ለችግርና ለልመና ይዳረጋሉ፡፡ ይህ ሁኔታ ከግለሰብ ፣ ቤተሰብና ማህበረሰብ አልፎ እንደ አገርም በምጣኔ ሀብት ላይ መጥፎ ጉዳት በማድረስ ከባድ ዋጋ ያስከፍላል፡፡ በተጨማሪም በሽታው የወረርሽኝ ባህሪ ስላለው በጥቂት ሰዓታትና ቀናት ውስጥ አያሌ ሰዎችን ስለሚያጠቃና ይህንም መቆጣጠር የግድ ስለሚሆን ለዚህ የሚያስፈልጉ የመድሃኒትና ሌሎች የህክምና ቁሳቁሶች ከፍተኛ ወጭን የሚጠይቁ ስለሚሆኑ የጤናው ሴክተር ሙሉ ትኩረትን እዚሁ ላይ እንዲያርፍ በማድረግ ሌሎች የጤና አገልግሎቶች ትኩረት እንዳያገኙና ተደራሽነታቸውም ውስን እንዲሆን ያደርጋል ፤ ብለዋል።

ኮሌራ እንደ አለም፣ኢትዮጵያና አማራ ክልል ያለበትን ነባራዊ ሁኔታ እንዲነግሩን ሌላው ለሲስተር ሰፊ ያቀረብንላቸው ጥያቄ ነበር። በምላሻቸውም “ኮሌራ በብዙ የአለም ክፍሎች በተለይም በቂ የንጽህና አጠባበቅና የንጹህ ውሃ መሰረተ ልማት ተደራሽነት ችግር ባለባቸው ክፍሎች አሁንም አሳሳቢ የህዝብ ጤና ስጋት ነው፡፡ እነዚህን መሰረተ ልማቶች ባሟሉ የበለፀጉ አገሮች ዘንድ ደግሞ ለሽታው መነሻ ምቹ ጉዳዮች ተብለው ከላይ የተገለጹት ችግርነታቸው ዜሮ ደረጃ ላይ ያሉ ናቸው፡፡ በሪፖርት ልዩነትና ጣልቃ ገብነቶች ምክንያት የቅርብ ጊዜ መረጃ ሊለያይ የሚችል ቢሆንም የዓለም ጤና ድርጅት ዘገባ እንደሚያመለክተው በየዓመቱ ከአንድ ነጥብ ሶስት እስከ አራት ሚሊዮን የሚደርሱ የኮሌራ በሽታዎች በአለም አቀፍ ደረጃ ይከሰታል፤በሎቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችም ይሞታሉ።

በአፍሪካም የኮሌራ በሽታ ስርጭት ከመቸውም ጊዜ በከፋ ሁኔታ እየጨመረ ይገኛል፡፡ አህጉሩ ለኮሌራ በሽታ መከሰት ምቹ ሁኔታዎች ያሉበት ክፍል እንደመሆኑ መጠን በበሽታው የሚጠቁ ህዝቦች ቁጥራቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ንፁህ የመጠጥ ውሃ እጥረትና የንጽህና ጉድለት የአፍሪካ አህጉር መገለጫዎች ናቸው፡፡ እነዚህ መገለጫዎች ደግሞ የኮሌራ በሽታ ዋነኛ መከሰቻ መንስኤዎች ከመሆናቸው አንጻር በርካታ የአፍሪካ ሀገሮች በዚህ ወረርሽኝ በየጊዜው ይጠቃሉ፡፡ አያሌ ሰዎችም በበሽታው ይሞታሉ፡፡ ኢትዮጵያ አንዷ የአፍሪካ ሀገር እንደመሆኗ መጠን ለኮሌራ ወረርሽኝ ተጋላጭ ናት፡፡ ለኮሌራ ወረርሽኝ መከሰት ምቹ ሁኔታዎች ተብለው እንደ አፍሪካ የተጠቀሱት ጉዳዩች የኢትዩጵያም መገለጫዎች ናቸው፡፡ በሽታው ምቹ ሁኔታዎችን እየጠበቀ በመከሰት በርካታ ኢትዩያዊያንን ያጠቃል፡፡ ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉትም ለሞት ይዳረጋሉ፡፡

በኢትዮጵያ ኮሌራ “አተት” ተብሎ ለብዙ ዓመታት ሲጠራ ቆይቷል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ኮሌራ ተብሎ ከተጠራ ከውጭ አገር የሚመጡ ቱሪስቶች ቁጥር ይቀንሳል የሚል ስጋት ስለነበር ነው፡፡ “አተት” ምህፃረ ቃል ሲሆን አ = አጣዳፊ ፣ ተ= ተቅማጥ ፣ ት = ትውከት የሚል በኮሌራ ዋና ዋና

ምልክቶች የተሰየመ ስያሜ ነው እንጅ በትክክለኛ ሳይንሳዊ ስሙ ኮሌራ ተብሎ ይጠራል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ "አተት" የሚለው መጠሪያ ቀርቶ "ኮሌራ" በሚለው ዋና መጠሪያው ነው በሚዲያና በህትመት እየወጣ ያለው፡፡ ይሁን እንጅ ህብረተሰቡ "አተት" በሚለው ስያሜው ለረጅም ጊዜ ስለሚያውቁት ኮሌራ የሚለውን መጠቀም ላይ ሲደናገሩ ይስተዋላል፤ በለመዱት "አተት" ብለው ቢጠሩትም የሚያመጣው ችግር እንደሌለ ልብ ይሏል፡፡ ቢሆንም ዋናው ቁም ነገር ምልክቶችን አውቀው ወደ ህክምና በመሄድ ራሳቸውን ከሞት እንዲያተርፉ መገንዘባቸው ነው እንጅ "አተት" ወይም ኮሌራ ብለው መጥራቱ ላይ አይደለም፡፡

እንደ አማራ ክልል ያለው የበሽታው ተጨባጭ ሁኔታም እንደ ኢትዮጵያ ካለው የተለየ አይደለም፡፡ ላለፉት ሁለት አስርት ዓመታት የክልሉ የጤና ችግር ሆኖ ቆይቷል፡፡ ይህ የሆነበት ደግሞ በክልሉ ለኮሌራ ወረርሽኝ መከሰት ምቹ የሆኑ ሁኔታዎች ስላሉ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅትም በክልሉ በርካታ አካባቢዎች እየተከሰተ ጉዳት በማድረስ ላይ ይገኛል። ለምሳሌ በምዕራብ ጎንደር ዞን ቋራ ወረዳ፣በሰሜን ጐጃም ዞን፣ባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ፣በባህር ዳር ከተማ፣በአዊ ብሄረሰብ አስተዳደር ጃዊ ወረዳ፣እና በምዕራብ ጐጃም ዞን ቡሬ ከተማ በሽታው ተከስቶ ነበር፡፡ በእነዚህና ሌሎች አካባቢዎች ያለው መረጃ እንደሚጠቁመው በሺዎች የሚቆጠሩ ህሙማን ሪፖርት ተደርጓል፡፡ ከእነዚህ ህሙማን መካከል ይህን ያህል ሰዎች ለሞት ተዳርገዋል ብሎ በአህዛዊ መረጃ ለመግለጽ በተለያዩ ምክንያቶች ባይቻልም ለሞት የተዳረጉ ሰዎችም አሉ፡፡ እንደሚታወቀው ኮሌራ ቶሎ ህክምና ከተደረገለት የሚድን ስለሆነ የሟቾችን ቁጥር ዜሮ ማድረግም ይቻላል፡፡ ይሁን እንጅ አስፈላጊ ጥንቃቄዎችን ባለማድረግ፣ ይሻለናል በሚል ቤት ውስጥ ቁጭ ማለት፣ ቶሎ ወደ ህክምና መጥቶ የባለሙያዎችን እገዛና ተገቢውን ህክምና አለማግኘትና በሽታው በሰዓታት ውስጥ ገዳይ መሆኑ፤ ሚሉት ችግሮች ተደማምረው ብዙዎች ህይዎታቸውን ያጣሉ፤ በማለት ያቀረብንላቸውን ጥያቄ በሰፊው አብራርተውልናል።

ኮሌራ በተለየ ሁኔታ የሚከሰትባቸው ወቅቶችና አካባቢዎች አሉ ፤ የሚል ግንዛቤ በማህበረሰቡ ውስጥ አለና ይህ ምን ያህል ትክክል ነው? የሚለውንም በቃለ መጠይቁ ወቅት አንስተንላቸው ነበር፡፡ ግንዛቤው መኖሩን ጠቁመው ፤ ግን ትክክል አይደለም ብለዋል። በማስረጃ አስደግፈው ሲያብራሩም በሽታው ለመቀስቀስ ምቹ ሁኔታዎችን እስካገኘ ድረስ በማንኛውም ወቅትና አካባቢ(በበጋ ፣ በክረምት ፣ በገጠር ፣ በከተማ ፣ ወዘተ) ሊከሰት እንደሚችል ጠቁመዋል። ይሁን እንጅ ክረምት ላይ ወረርሽኙ በከፍተኛ መጠን የሚጨምርበት ሁኔታ አለ፡፡ ይህም የሚሆነው ክረምት የዝናብ ወቅት እንደመሆኑ መጠን ጎርፍ ስለሚኖር ቆሻሻን ወደ መጠጥ ውሃው እንዲገባ በማድረግ እንዲቆሸሽ ያደርጋል። የተበከለ ወይም የቆሸሸ ውሃ ደግሞ ለኮሌራ በሽታ መከሰት ዋነኛ ምክንያትና አንዱ ምቹ ሁኔታ ነው፡፡ በበጋ ወቅትም ቢሆን ኮሌራ በመፀዳጃ ቤት አለመኖር ምክንያት በየቦታው መፀዳዳት ካለ ወይም ደግሞ መፀዳጃ ቤት ኖሮ ንጽህናው የማይጠበቅ ከሆነ ዝንቦች በዚያ አካባቢ ቆይተው ወደ ቤት በመምጣት በምግብ ላይ በማረፍ በኮሌራ አምጭ ባክቴሪያዎች በመበከል ሰዎች በበሽታው ይያዛሉ ፤ በማለት የተለዬ ወቅት እንደሌለው አስረድተዋል።

ወደ ፀበል ቦታዎች ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሰዎች ለጸበል ይጓዛሉ። በተለያዩ አደጋዎች የተፈናቀሉ በሺዎችና በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ስደተኞችም በመጠለያ ጣቢያዎች ተጠጋግተው ይኖራሉ። ወደ ሰፋፊ የእርሻ ቦታዎች ደግሞ አያሌ የቀን ሰራተኞች እንዲሁ ይሄዳሉ። እነዚህ አካባቢዎች ይህን ያህል ቁጥር ያለው ህዝብ ሊያስተናግዱ የሚችሉ ንጹህ የመጠጥ ውሃና የንጽህና መጠበቂያ መሰረተ ልማቶች ስለማይኖራቸው የቆሸሸ ውሃ መጠጣትና በየቦታው መጸዳዳት ስለሚበዛ ወረርሽኙ ምቹ ሁኔታ አግኝቶ እንዲከሰትና ሰዎች እንዲጎዱ ያደርጋል፡፡ በድርቅ የተጎዱ ውሃ አጠር አካባቢዎችም ንጹህ የመጠጥ ውሃ ችግር ስለሚያጋጥማቸው በሽታው በአብዛኛው ይከሰታል፡፡ ይህ ሲባል ግን ኮሌራ የሚከሰትባቸው የተለዩ ቦታዎች ናቸው ማለት አይደለም። ንጹህ የመጠጥ ውሃና ንጽህና መጠበቂያ መሰረተ ልማቶች በተሟሉላቸው ከተሞች አካባቢም ሊከሰት እንደሚችል በማስረገጥ ኮሌራ የሚከሰትበት የተለዬ ቦታ እንደሌለው ተጠየቃዊ በሆነ መልኩ አብራርተዋል።

ውድ አንባቢዎቻችን እስኪ አሁን ደግሞ የኮሌራ በሽታን የትኩረት ጉዳዩ አድርጎ እየሰራ የሚገኘው የአማራ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት በበሽታው ዙሪያ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ እንመልከት። ሲስተር ሰፊ ይህን ጉዳይ አስመልክቶ ሲገልፁ፡- ኮሌራ በየትኛውም ወቅትና አካባቢ ሊከሰት እንደሚችል ስለሚታወቅ ኢንስቲቱዩቱ መሰራት ያለባቸውን ቅድመና ድህረ ተግባራት ለይቶ የቅድመ ዝግጅት እቅድ ያቅዳል ብለዋል፡፡ እቅዱ የመከላከልና የመቆጣጠር ተግባራትን የሚይዝ ሲሆን መሬት ሲነካ ቀድሞ በመከላከል እንዳይከሰት ማድረግ የሚያስችሉ ተግባራት ትኩረት ተሰጥቷቸው ይከናወናሉ፡፡ እነዚህ ተግባራት ደግሞ ቀደም ሲል የኮሌራ በሽታ መከላከያ መንገዶች ተብለው ከላይ የተዘረዘሩት መሆናቸውን አስታውሰዋል። በሽታው ከመከላከል አቅም በላይ ሆኖ ቢከሰት ኢንስቲትዩቱ በመጀመሪያ በሽታውን ቶሎ በመለየትና በላቦራቶሪ እንዲረጋገጥ በማድረግ መከናወን ካለባቸው የመቆጣጠሪያ ተግባራት ዋና የሆነውን ህክምና ቶሎ እንዲሰጥ ያዝዛል ፣ ያስተባብራል ፣ ይከታተላል። የህክምና መድሃኒትና ቁሳቁሶች በበቂ ሁኔታ እንዲኖሩ ያደርጋል። ኢንስቲትዩቱ እንደ ጤና ቢሮና ውሃ ቢሮ ያሉትን ሴክተር መስሪያ ቤቶች በማስተባበር ኮሌራ በተከሰተባቸው አካባቢዎች የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት እንዲኖር ፣ መፀዳጃ ቤቶች እንዲዘጋጁ ፣ የውሃ ማከሚያ ኬሚካሎች እንዲደርሱ ይሰራል፡፡ በተመሳሳይ አጋር አካላት በኮሌራ ለታመሙ ሰዎች ማከሚያ የሚውሉ እንደ መድሃኒት ያሉ ግብዓቶችን እዚያው ድርስ እንዲያቀርቡ ያስተባብራል በማለት የኢንስቲትዩቱን ተግባርና ሀላፊነት ዘርዝረዋል፡፡

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ኮሌራ እንደ አማራ ክልል ያለበት ሁኔታ የሚያሳየው የጤና ችግር ወይም ደግሞ ስጋት ሆኖ መቀጠሉን ነው። ይህ እንዳይሆን ማድረግ ያልተቻለው በሽታው የማይጠፋ ሆኖ ነው? ወይስ ግለሰብ፣ ህብረተሰብ፣ ተቋማት ፣ መንግስት ፣ ወዘተ. ለበሽታው ትኩረት ያለመስጠት ነው ወይ?

የሚለው መነሳት ያለበት ጉዳይ ነው። ሲስተር ሰፊ ለዚህም ምላሽ የሰጡት መዘናጋት፣የሀላፊነትና የባለቤትነት ስሜት አለመኖር እና የግንዛቤ ማነስ የሚሉ ጉዳዮችን አንስተው በማብራራት ነው።

ኮሌራ ምቹ ሁኔታዎችን እስካገኘ ድረስ በማንኛውም ወቅትና አካባቢ የሚከሰት መሆኑን አውቆ በንቃት መጠበቅ ወይም ሁል ጊዜ ዝግጁ መሆን ያስፈልጋል፡፡ ይህንም እንደ አንድ የሕይወት ክህሎት ወስዶ ማዳበር ይገባ ነበር። ይሁን እንጅ ያ ሁሉ ተዘንግቶ ይቆይና በሽታው ተከሰተ ሲባል ሁሉም ነገር ከዜሮ ይጀመራል። በሽታውን ለመቆጣጠር የሚያስፈልገውን የፋይናንስ ፣ የቁሳቁስ ፣ የሰው ሀይል ማደራጀት ፣ ወዘተ. ዝግጁ ለማድረግ ብዙ ጊዜ ይፈጃል። እንደሚታወቀው ኮሌራ ደግሞ ቶሎ ህክምና ካልተሰጠው በሰዓታት ውስጥ ለሞት የሚዳርግ በሽታ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ መዘግየት ካለ በፍጥነት መቆጣጠር ስለማይቻል የሚጠቁት ሰዎች ቁጥር ያሻቅብና ከቁጥጥር ውጭ የመሆን እድል ይኖረዋል ፤ ለሞት የሚዳረጉትም እንዲሁ ቁጥራቸው ይጨምራል። ስለዚህ “መዘናጋት ይቁም” የሚል ምክር ለሚመለከታቸው አካላት በማሳሰብ ጉዳዩን አብራርተዋል።

ኮሌራን ጨርሶ ማጥፋት እንኳን ባይቻል የመከሰት ደረጃውን ዜሮ ላይ እንዲቆይ ማድረግ ይቻላል። ይህም ሊፈፀም የሚችለው በተባበሩ ክንዶች ሲመከት ነው። በአጠቃላይ የጤና ሴክተሩ ወይም የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ተቋም ብቻውን የሚከታተለውና የሚቆጣጠረው በሽታ አይደለም፡፡ ግለሰብ ፣ ቤተሰብ ፣ ማህበረሰብ ፣ ድርጅት ፣ተቋም ፣ ወዘተ. እንደሚመለከተው አውቆ ሀላፊነቱን መወጣት ይኖርበታል፤ ብለዋል።

ኮሌራ በተመቸው ጊዜና ቦታ እየተከሰተ ሰዎችን የሚያጠቃውና ለሞት የሚዳርገው በግንዛቤ ማነስ ወይም ደግሞ ጨርሶ ግንዛቤ ባለመኖር ነው፡፡ ህብረተሰቡ ስለበሽታው አጠቃላይ ሁኔታ ወጥ የሆነ ግንዛቤ መያዝ ላይ ክፍተት አለ፡፡ የሚሰጣቸውን ትምህርት ቶሎ የሚረዱ ግን ደግሞ ተግባራዊ የማያደርጉ እና ጭራሽ የመረዳት ችግር ያለባቸው ሰዎች ቁጥር አያሌ ነው፡፡ ለዚህ ማሳያ የሚሆነው ወረርሽኙ ወደ አለባቸው አካባቢዎች አትሂዱ ተብለው እየተነገሩ የማይቀበሉ ጭራሽ አውቃችሁ ነው፤ እያሉ የሚሞግቱ ሰዎች ብዙ ናቸው። በሌላ በኩል ጥሩ ግንዛቤ ኖሯቸው የሚጠነቀቁ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል የህብረተሰብ ክፍሎች ያሉ ቢሆንም ተጨምቆ ሲታይ እንዲህ አይነት ጉራማይሌ ግንዛቤ ያለው ህብረተሰብ በበሽታው የመጠቃት እድሉ ሰፊ እንደሚሆን መገመት አይከብድም፡፡ ግንዛቤው ዝቅተኛ የሆነ ህብረተሰብ የባለቤትነት ስሜት ስለማይኖረው ራሱን ከኮሌራ አይከላከልም፤አለፍ ሲልም ከጤና ኢንስቲትዩቱ ጎን አይሰለፍም፡፡ ይህ ሁሉ ክፍተት የሚያመለክተው የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ ላይ ወደፊት ብዙ መስራት እንደሚገባ ነው፤ካሉ በኋላ እንዴት ይሰራ የሚለውንም ቀጥለው አብራርተውታል።

የፊት ለፊት ውይይት መድረኮችን በመጠቀም ኮሌራን መሰረት ያደረገ በተለይ በብዛት ይከሰትባቸዋል ተብለው በተለዩት የክልሉ አካባቢዎች አማራ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ከጤና ቢሮ ጋር በመሆን ተንቀሳቃሽ የህክምና ቡድን በመመደብ ህዝቡ ራሱን እንዲከላከል የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ይሰጣል። ክልል ላይ መድረኮችን አዘጋጅቶ የሀይማኖት አባቶችን በመጥራት ከጤናው ሴክተር ጋር በመመካከር ለመቆጣጠር ምን መደረግ አለበት የሚለውንና እነሱም የድርሻቸውን እንዲወጡ የሚያስገነዝብ ውጤታማ ውይይቶች ተደርገዋል፤ወደፊትም ይካሄዳሉ። ሌላው የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራው ማሳለጫ ዘዴ ሆነው እያገለገሉ የሚገኙት የህትመት ውጤቶች ናቸው፡፡ የአማራ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት በራሪ ወረቀትና መጽሄት አሳትሞ የጸበል አገልግሎት ወደ ሚሰጥባቸው የኦርቶዶክስ ሀይማኖት ቤተክርስቲያናት በመላክ የሀይማኖት አባቶች በአውደ ምህረት ላይ ስብከት ሲሰጡ አብረው ለምዕመናንና ለተሰባሰቡት ፀበልተኞች ስለኮሌራ አጠቃላይ ሁኔታ በማስተማር እንዳይከሰት እንዲከላከሉ ከተከሰተ ደግሞ ቶሎ ወደ ህክምና መሄድ እንዳለባቸው የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራው ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ህብረተሰቡን በማሳወቅ፣ በማስተማር፣ በማሳመን፣ በማሳሰብና በማነሳሳት ግንዛቤን በማሳደግ በኩል ጉልህ ድርሻ አለው። ሬዲዮ እና ቴሌቪዥን ለዚህ ሚዲያ አይነት ጥሩ አብነቶች ሲሆኑ ኮሌራ በክልሉ የት የት አካባቢ አለ? ወረርሽኙ ያለበት ሁኔታ ምን ይመስላል? የሚሉትንና ሌሎች ቁልፍ መልዕክቶችን ከአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን ጋር ተባብሮ በማስተላለፍ ማህበረሰቡ አውቆ ጥንቃቄ እንዲያደርግ ግንዛቤ ማስጨበጥ ስራው ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ አብዛኛውን የክልሉ ህዝብ ተደራሽ በማድረግ በኩል ሬዲዮ ተመራጭ መሆኑ ታምኖበት ከአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን የአየር ሰዓት ተወስዶ በሳምንት አንድ ቀን ሀሙስ ከስምንት እስከ 10 ሰዓት “ምን እናማክርለዎት” በሬዲዮ የኮሌራ ቁልፍ መልዕክቶችን በማስተላለፍ በኩል እየተሰራ ነው፡፡ እንዲሁም በቴሌቪዥን “ምክር ከሀኪምዎ” እሁድ ቀን ከ10 እስከ 11 ሰዓት በወቅታዊ የኮሌራ ዝግጅቶች ላይ ሃላፊዎች ወይም ባለሙያዎች እየተጋበዙ ግንዛቤ ያስጨብጣሉ፡፡ እንደ “ቲክቶክ” እና “ፌስቡክ” ያሉ ማህበራዊ ሚዲያዎችን ሳይቀር ከአሚኮ ጋር በትብብር በመስራት ለግንዛቤ ማስጨበጫ ስራው እያገለገሉ ይገኛሉ፡፡ የግል ሚዲያዎች ለአብነት ያህል ሀገሬ ቲቪ፣አሀዱ ቲቪ፤ ከአለም አቀፍ ሚዲያዎች እንደ የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ እና የጀርመን ድምጽ ሬዲዮ ባሉት ደግሞ ሃላፊዎችና ባለሙያዎች ቀጥታ እየቀረቡ ስለኮሌራ በሽታ መልዕክት ያስተላልፋሉ፤ግንዛቤ ማስጨበጫ መረጃዎችን ያሰራጫሉ፤ብለዋል። እዚህ ላይ መነሳት ያለበት ጉዳይ በእነዚህ ዘዴዎች ሁሉ በተሰሩት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ህብረተሰቡ ስለ ኮሌራ በሽታ ያመጣው የአመለካከት ለውጥ ምን ይመስላል የሚለው ይሆናል፡፡ የአመለካከት ለውጥ አዕምሯዊና ውስጣዊ ባህሪ ስላለው በደፈናው ለውጥ መጥቷል ብሎ መናገር ያስቸግራል፡፡ በመሆኑም ይህ ጥያቄ የሚመለሰው ሳይንሳዊ የሆነውን የጥናት መንገድ በመከተል ቢሆን የተሻለ ተቀባይነት ያለው ይሆናል፡፡ ጥናቱ ከሀይማኖት አባቶች፣ ከፀበልተኞች ፣ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ ከአጋር አካላት፣ በአጠቃላይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ኮሌራ የሚያጠቃቸውና የስራ ንክኪ ካላቸው ግለሰቦች ፣ ድርጅቶች ፣ ተቋማት ፣ ወዘተ. የጥናት መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም ክልል ወካይ ሆኖ ቢጠና የክልሉ ህዝብ ስለኮሌራ በሽታ ያለው አመለካከት በምን

ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ማወቅ ያስችላል። ክፍተቶችንም ለይቶ ለቀጣይ እርምጃዎች ለመዘጋጀት ትልቅ አቅም ይፈጥራል። የአማራ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩትም ይህን ግንዛቤ ውስጥ ባስገባ መልኩ ጥናቱን ማካሄድ መጀመሩን ጠቁመዋል።

በመጨረሻም እንደ መውጫ ያቀረብንላቸው ጥያቄ ለኮሌራ በሽታ ዘለቄታዊ መፍትሄ ለማምጣት በመንግስት በኩል እየተደረጉ ያሉት ጥረቶች እንደተጠበቁ ሆነው የሌሎች አጋር አካላት ሁለንተናዊ ተሳትፎም አስፈላጊ ነውና በበሽታው ዙሪያ እገዛ የሚያደርጉ እነማን እንደሆኑና ምን እየሰሩ እንደሆነ እንዲገልጹልን ነው፡፡ እሳቸውም ጉዳዩን ሲያብራሩ “የኮሌራ በሽታ ከባህሪው አስቸጋሪነት አንጻር ትልቅ የበጀት አቅም፣ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር፣ጊዜና ትኩረት ተሰጥቶት በባለቤትነት መስራትን ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም የአማራ ህብረተሰብ ጤና ኢንስትዩት ብቻውን በሚያደርገው ጥረት ለበሽታው ዘለቄታዊ መፍትሄ ማበጀት ስለሚቸገር ሴክተር መ/ቤቶችን፣መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እና የሀይማኖት ተቋማትን በተለይ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንን አጋር አካል አድርጎ በማስተባበር እየሰራ ይገኛል፡፡ እነዚህ አካላት በኮሌራ ዙሪያ ገብተው እንዲሰሩ ኢንስቲትዩቱ በትብብር የሚያሰራ ግንኙነት ከመፍጠር ጀምሮ በበሽታው ዙሪያ መስራት ስለሚፈቀድላቸው ዝርዝር ጉዳዮች በቂ መረጃ እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ በዚህ መሰረት አጋር አካላት ሊሰሩ የሚፈልጉትን ጉዳይ ለይተው እንስራ ብለው ሲመጡ ፈቃድ ይሰጣቸዋል፡፡ ይህ ሁሉ ጥረት ዘለቄታዊ መፍትሄ በማበጀት የኮሌራን የመቀስቀስ ሀይል ዜሮ በማድረግ የክልሉ ህዝብ በሽታው ከሚያደርስበት ስቃይ እፎይ እንዲል ነው፡፡ እንደሚታወቀው ኮሌራ እንዲቀሰቀስ የሚያደርጉት ዋነኛ መንስኤዎች አሉ፡፡ እነዚያ መንስኤዎች መወገድ ያለባቸው ከተወገዱና መሟላት ያለባቸውም ከተሟሉ ለበሽታው ዘለቄታዊ መፍትሄ ተበጀለት ማለት ነው፡፡ ይህንም ለመፈፀም ነው እንግዲህ አጋር አካላትን ከጎን ማሰለፍ ያስፈለገው። የአለም ጤና ድርጅት፣ ፕላን ኢንተርናሽናል ፣ ዩኒሴፍ እና ኤም.ኤስ.ኤፍ ሆላንድ የተባሉ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በአጋርነት የሚሰሩ ሲሆን የኮሌራ በሽታ መድሀኒቶችን በማቅረብ፣የውሃ ማስተላለፊያ ቧንቧ መስመሮችን በመዘርጋት፤ የመጸዳጃ ቤት ግንባታዎችን በበጀት በማገዝ፣ ንጹህ ውሀ በማቅረብ፣ የህክምና ቁሳቁችን እንደ ድንኳን፣ አልጋ የመሳሰሉትን በማቅረብ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ሲያበረክቱ ቆይተዋል፡፡ በተለይ የዘለቄታዊ መፍትሄው ቁልፍ ጉዳይ የሆኑትን የንፁህ መጠጥ ውሃና የመፀዳጃ መሰረተ ልማቶችን በመገንባት ኮሌራን በጽናት ታግለዋል። ቤተክርስቲያንም በተመሳሳይ ለኮሌራ በሽታ ዘለቄታዊ መፍትሄ ለማበጀት በሚደረገው ርብርብ አጋር አካል ናት። በሽታው በተደጋጋሚ የሚከሰትባቸው የፀበል ቦታዎች የሚገኙት በተለያዩ ቤተ ክርስቲያናት አካባቢ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ፀበልተኞች ወደዚያ ሄደው ይቆያሉ። በመሆኑም እነዚህ ቦታዎች ላይ ሁለት ወሳኝ ስራዎች መከናወን አለባቸው። የመጀመሪያው የሀይማኖት አባቶች ለፀበልተኞች ስለኮሌራ በሽታ ትምህርት በመስጠት መከላከል ላይ ትኩረት በማድረግ ራሳቸውን ከበሽታው እንዲከላከሉ ግንዛቤያቸውን ማዳበር ያስፈልጋል። ሁለተኛው ቁልፍ ተግባር የንጹህ መጠጥ ውሀና የመጸዳጃ ቤት አገልግሎት የሚሰጡ መሰረተ ልማቶች እንዲኖሩ ማድረግ ነው፡፡ ፀበል ቦታዎች ላይ ኮሌራ በሽታ በተደጋጋሚ የሚከሰተው በዋናነት በእነዚህ መሰረተ ልማቶች አለመሟላት ነው። በመሆኑም ቤተ ክርስቲያናቱ በራሳቸው መንገድ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት የንፁህ መጠጥ ውሃና የመፀዳጃ ቤት አገልግሎቶችን ድጋፍ ጠይቀው በማስገንባት በቋሚነት እንዲኖራቸው ማድረግ አለባቸው። ከሴክተር መስሪያ ቤቶች ጋርም እንዲሁ በትብብር የሚያሰራ ጠንካራ ግንኙነት በመመስረት ለኮሌራ በሽታ ዘለቄታዊ መፍትሄ በማበጀት አጋርነታቸውን ማስመስከር ይኖርባቸዋል።

ሴክተር መስሪያ ቤቶችም ለበሽታው መፍትሄ በማፈላለጉ ጥረት ውስጥ ሃላፊነታቸውን በተግባር ማሳየት ይገባቸዋል። እነዚህ ተቋማት የኮሌራ በሽታን በባለቤትነት ከሚመራው አማራ ክልል የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ጋር በቅንጅት መስራት አለባቸው። ለምሳሌ እንደ ጤና ቢሮ እና ውሃ ቢሮ ያሉት ሴክተር መስሪያ ቤቶች ከኢንስቲትዩቱ ጋር በመቀናጀት ከኮሌራ በሽታ ጋር በሚያገናኟቸው ጉዳዮች ዙሪያ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እያበረከቱ ይገኛሉ። ቀደም ሲል እንደተገለፀው ኮሌራ በሽታ በንፁህ መጠጥ ውሃና በመፀዳጃ ቤት መሰረተ ልማቶች ላይ የተንጠለጠለ ህልውና ያለው ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ውሃ ቢሮ የውሃውን ጉዳይ እንዲሰራ ይደረጋል። ጤና ቢሮ ደግሞ የመፀዳጃ ቤት መሰረተ ልማቱን ይሰራል። በዚህ መልኩ ሌሎች አስፈላጊ ናቸው የሚባሉት ሴክተር መስሪያ ቤቶችም ተገምግመው በኮሌራ ዙሪያ ባሉ ክፍተቶች ገብተው እንዲሰሩ ፈቃድ ይሰጣቸዋል። ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ የአማራ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩትም አጋር አካላትን በማስተባበር፣ ፈቃድ በመስጠት ፣ በማማከር፣ በመምራትና በመከታተል ለኮሌራ በሽታ ዘለቄታዊ መፍትሄ የሚበጁ ማለፊያ ስራዎችን እንዲፈጽሙ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ ይኖርበታል ፤ በማለት የአጋር አካላትን ሚና እና ከኢንስቲትዩቱ ጋር ያላቸውን የግንኙነት አግባብ በሰፊው አብራርተውልናል።

ሲስተር ሰፊ ደርብ በመልዕክታቸው ማህበረሰቡ ኮሌራ የሚያዳርስበትን ሁለንተናዊ ጉዳት መቀነስ እንዲችል የበሽታውን መከላከያ መንገዶች በአግባቡ መተግበር ይገባዋል። ይህ በሽታው ከመከሰቱ በፊት አስቀድሞ መወሰድ ያለበት እርምጃ ስለሆነ በሽታው የሚያስከፍለውን ዋጋ በእጅጉ ይቀንሰዋል። ቀደም ሲል እንደተገለፀው የኮሌራ ወረርሽኝን አንድ ተቋም ብቻውን ሰርቶ ሊከላከለው ወይም ሊቆጣጠረው ስለማይችል ህብረተሰቡ ከጤና ሴክተሩ ጎን ሆኖ መስራት ይኖርበታል። ሌላው ቁልፍ ጉዳይ ለኮሌራ መነሻ ምቹ ከሆኑት ሁኔታዎች መካከል በተለይ የንጹህ ውሃ መጠጥና የመጸዳጃ ቤት አቅርቦት የግድ ለህብረተሰቡ ሊሟሉለት ይገባል፤ የሚለውን በማስተላለፍ ሀሳባቸውን ቋጭተዋል፡፡

እኛም መረጃ በመስጠት የተባበሩንን ሁሉ እያመሰገን የኮሌራ በሽታ መንስኤዎች፣ ምልክቶች፣መከላከያ መንገዶች፣ህክምናው፣እንደ አማራ ክልል ያለበትን ሁኔታና አጋር አካላት ያደረጉትን አስተዋፅኦ የዳሰስንበትን ጥንቅር በዚህ ቋጨን - ሰላም!

# ዳግም ልደት የሚሻው ጥበብ

በደፋሩ እምሬ

ከሰው ልጅ ዝግመተ ለውጥ ጋር አብሮ የቆየ፣የሰው ልጅ በዋሻ ይኖር በነበረበት ዘመን የተጀመረና ከጥበብ ስራዎች ሁሉ ቀዳሚ ነው፡፡ የሰው ልጅ ከዋሻ ሲወጣም አብሮ ወጥቶ እየተራቀቀና የበለጠ ተወዳጅ እየሆነ ዘመንና ትውልድን አብሮ ተሻግሯል፡፡ ብርቅየነታቸውና ተወዳጅነታቸው የማይደበዝዙ የምድራችን የምንጊዜም ምርጥ ስራዎችንና ባለሙያዎችን ያበረከተ የጥበብ ዘርፍ ነው፤ ስነ-ስዕል፡፡

ስነ-ስዕል የተጀመረበት ዘመን እንደ መጀመሪያ ውልደት ተወስዶ፣ አደገ፣ከዚያም ሞተ የሚል አይነት የህይወት ኡደት ውስጥ በማለፍ ላይ ያለ ይመስላል፡፡ እጅግ በጣም አደገ፣ ተመነደገ አምሮበት ኖረ የሚባልበት “ዘመነ ዳግም ልደት” ወይም “ዘመነ ህዳሴ” እያሉ በአማረኛው ይጠሩታል፤ በእንግሊዘኛው ‘Renaissance’ የሚባለው ነው፡፡ ከ14ኛው እስከ 17ኛው ክፍለ ዘመን ያለውን መካከለኛ ጊዜ ይወክላል፡፡ ከዚህ በኋላ የቀጠለው ዘመናዊው ዘመን ሲሆን ሳይንሳዊ አስተሳሰብ እየዳበረ በመሄዱ ቴክኖሎጅዎች እየተፈጠሩ ቀጥለው ዛሬ የተራቀቀው ዘመን ላይ ደርሷል፡፡ ይህ ዘመናዊ ዘመን ስነ ስዕል ለተባለው የጥበብ ዘርፍ የመረሳት፣ የመገፋት፣ ተወዳጅነቱን የማደብዘዝና ትኩረት የማሳጣት አደጋ የደቀነበት ሁኔታ ይስተዋላል፡፡ ስለሆነም ይህ ጉዳይ ለምን ሊሆን ቻለ? የሚል መመርመር የሚገባው ጥያቄ መሆኑ ስለታመነበት ለዚህና ለሌሎች ተጨማሪ ተያያዥ ጥያቄዎች ለምሳሌ ስለስዕል ታሪካዊ አመጠጥና እድገት፣ ስለ ስዕል ባህሪትና ፋይዳ፣እንደ ኢትዮጵና አማራ ክልል ያለበት ሁኔታ፣ በአሁኑ ወቅት ለስዕል ጥበቡ ተግዳሮቶች ምን እንደሆኑ፣ወዘተ. በባለሙያ ምላሽ ለማሰጠት ወደ ታሪካዊቷ ጎንደር ከተማ ተጉዘን በከተማዋ የሚገኘው የዞብል የስዕልና ቅርፃ ቅርፅ ማህበር ስራ አስኪያጅ፣ ሰዓሊና አሰልጣኝ የሆኑት ወጣት ዳዊት አበባው የሰጡንን መረጃ ለዚህ አምድ በሚመች መልኩ አቀናብረን አቅርበነዋል-መልካም ንባብ፡፡



ሰዓሊ ዳዊት አበባው በስዕል ስራ ላይ

ስዕል ለአይን እንዲታይ ተደርጎ በወረቀት፣ በሸራ፣ በግድግዳ፣ ወዘተ. ላይ በእርሳስ፣ በብሩሽ፣ በብዕር፣ የተሰራ፣ የተነደፈ ወይም ከጠጣር ነገር የተቀረፀ የአንድ ነገር ወይም ሃሳብ መልክና ምስል ነው በማለት ገለጻቸውን የጀመሩት ወጣት ዳዊት፡- ዞብል የስዕልና ቅርጻ ቅርጽ ማህበር ፋሲል ግንብ መዋኛ ግቢ ውስጥ እንደሚገኝና እዚህ ቦታ ላይ እንዲሆን የተደረገውም በቱሪስቶች በተደጋጋሚ የሚጎበኝ መዳረሻ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በስዕልና ቅርጻ ቅርጽ አማካኝነት የጎንደር ከተማንና አካባቢውን እምቅ መስህብ ለማስተዋወቅ በብዙ መመዘኛ ምቹ መሆኑ ታምኖበት ነው ብለዋል፡፡ “ ነገርን ነገር ያነሳዋል” እንዲሉ አበው እኛም እሳቸው ከሰጡት ሀሳብ ተነስተን፡-ማህበሩን ማቋቋም ለምን እንዳስፈለገ፣ስለአባላቱና ምን ላይ አተኩረው እንደሚሰሉ እንዲያብራሩልን ጠየቅናቸው፡፡ በምላሻቸውም የማህበሩ አባላት ስነ ስዕልና ቅርጻ ቅርጽን የሙሉ ቀን ሙያቸው አድርገው መስራት ስለሚፈልጉ ነው፤ ብለዋል፡፡

አባላት የስነ-ስዕልና ቅርጻ ቅርጽ ሙያቸውን ተጠቅመው የጎንደርን ነገስታት ታሪክ፣ ባህላዊ አመጋገብ፣አለባበስ፣ወዘተ. በመሳልና በመቅረጽ ለቱሪስቶች ማስተዋወቅ ላይ በዋናነት ያተኩራሉ፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን በዓላትና ኩነቶች እየተመረጡ አባላት የስዕል አውደ-ርዕዮችን ጎንደር ከተማ ውስጥ በማዘጋጀት የከተማው ነዋሪ የጎንደርን የቀደመ ታሪክና የመስህብ ሀብቶችን በማንበብና በሚዲያ ከሰማው ለየት ባለ መንገድ በስዕል አይቶ እንዲደሰትና እንዲረካ በማድረግ በኩል በንቃት ይሳተፋሉ፡፡ ማህበሩ አጫጭር ስልጠናዎችን የስዕል ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች፣ወጣቶች፣ወዘተ. እየሰጠም እንደሚገኝ የማህበሩ ስራ አስኪያጅ ተናግረዋል፡፡

የስዕል ጥበብ ፍላጐት፣ እይታ፣ ልምምድና እውቀት የመሳሰሉ መሠረታዊ ክህሎቶችን እንደሚፈልግም አጫውተውናል፡፡ ፍላጐት ወደ ስዕል ጥበብ ገብቶ ለመስራት ውስጣዊ ገፊ ሃይል ነው፡፡ ስዕል ዘው ብሎ የሚገባበት ዘርፍ ሳይሆን



“ይናገራል ስዕል እንዲሉ”ይህ ስዕል ምን እንደሚናገር ለራሳችሁ ንገሩ?

በፍላጐት ስለሚመራ ሰዓሊያን በዚያው ሰምጠው እንዲቀሩ ያደርጋቸዋል፡፡ ፍላጐት የወደፊት የህይወት መንገድ ወይም “መክሊት” የሚባለውን እጣ ፈንታና አቅጣጫም ይጠቁማል፡፡

የተለየ እይታ የሚባለው የስዕል ችሎታ ደግሞ ሰዓሊያን ነገሮችን የሚመለከቱበት አንግል (ማዕዘን) ነው፡፡ ሰዓሊያን የሚስሏቸው ስዕሎች ከሀሳብ ስለሚነሱና ሃሳቡንም በስዕል ለመግለፅ ከምን ማዕዘን ወይም እይታ አንፃር መሳል እንዳለባቸው መመልከቻ መነፀር ነው ማለት ይቻላል፡፡ ለአብነት ያህል አንድ ነጭ ልሙጥ ወረቀት ላይ ጠብ ያለች ጥቁር ቀለም ብትኖርና እይታችን እንድንገልፅ ብንጠየቅ አንዳችን ነጩን ወረቀት ብቻ ልናየው እንችላለን፤ ሌላችን ደግሞ ከወረቀቱ ይልቅ ትንሿ ጠብታ ጥቁር ቀለም ልትታየን ትችላለች፡፡ በመሆኑም ከትልቁ ነጭ ወረቀት ይልቅ ትንሿን ጠብ ያለች ጥቁር ቀለም ያየው የተሻለ ወይም የተለየ እይታ ያለው ይሆናል፡፡

ልምምድ በስዕል ስራ ላይ ለመሰማራት ወይም ሰዓሊ ለመሆን አስፈላጊ ክህሎት ነው፡፡ “ተግባራዊ ልምምድ ፍፁም ያደርጋል” እንደሚባለው በፍላጐቱ ተነሳስቶና ያለውን የተሻለ እይታ ይዞ በስዕል ጥበብ ውስጥ ጥሩ ሰዓሊ ለመሆን ብዙ ልምምዶች ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በጥበቡ አንቱ የተባሉ ሰዓሊ ለመሆን መውደቅና መነሳት እንዲሁም ረዘም ያለ ጊዜ እና ጉልበትን በልምምድ ማሳለፍ ይጠይቃል፡፡

ሌላው የስዕል ስራ በሳይንሳዊ እውቀት ሊመራ ይገባዋል፡፡ ትምህርት ቤት ገብቶ በመማር፣ በአጭርና በረዥም ስልጠና ወይም በሌላ አግባብ የስዕል ጥበብ እውቀትን አዳብሮ መገኘት ትልቅ አቅም ስለሚፈጥር ጥሩ ሰዓሊ ለመሆን እንደሚያስችልም ገልጸዋል፡፡

ከላይ የተገለጹት መሰረታዊ የስዕል ክህሎቶችን የታጠቁ አንቱ የተባሉ ወጣትና አንጋፋ ሰዓሊያን የሚስሏቸው ስዕሎች የበለጠ ይስባሉ ፤ ያስደስታሉ፡፡ ሙዚቃ ቋንቋ ነው እንደሚባለው ሁሉ ስዕልም ስሜትን መግለፅ የሚያስችል ስዕላዊ ቋንቋ ስለሆነ ይናገራል ፤ ይነበባል ፣ ያግባባል፡፡ “አንድ ስዕል ከበርካታ ቃላት በበለጠ ይናገራል” ሲባል የሚደመጠውም ለዚህ ነው ብለዋል፡፡

ወጣቱ ሰዓሊና የስዕል አሰልጣኝ ዳዊት አበበ የስዕል ረቂቅነት፣ ቁጥብነት፣ ሳቢነትና መልዕክት አስተላላፊነት የሚሉት መለያ ባህሪዎቹ እንደሆኑም አጫውተውናል፡፡ ቁጥብነቱ በበርካታ ቃላትና በብዙ ገጽ የወረቀት ላይ ፅሁፍ የሚተላለፍን መልዕክት በአንድ ስዕል መግለጽ ያስችላል፡፡ ቁጥብነቱ ከሚፈጀው ጊዜ ፣ ጉልበትና ወጭ አንፃርም ሊታይ ይችላል፡፡

ሌላው ባህሪው ደግሞ ረቂቅነቱ ሲሆን አንድን ስዕል አይቶ ምን እንደሚገልጽ ወይም ምን መልዕክት እንደሚያስተላልፍ ለመረዳት እስከሚያዳግት ድረስ ሰዓሊው የሚጠቀምበት የአሳሳል ጥበብ ነው፡፡ እንዲህ አይነት ባህሪ ተላብሰው የተሳሉ ስዕሎችን ተመልክቶ ለማንበብ ወይም ምን እንደሚናገሩ ለመረዳት የተለየ የእይታ ችሎታን ይጠይቃሉ፡፡

ሰዓሊያን በስዕል የደስታና የሀዘን ስሜትን ፣ የሰውን ልጅ የአኗኗር ዘይቤን ፣ አመጋገብን፣ አለባበስን፣ የአገር ፍቅርን፣ ተፈጥሮን፣ ጀግንነትን፣ የጦርነት አስከፊነትን፣ወዘተ. ይገልጹበታል፡፡ በአጭሩ በስዕል የማይገለጽ ነገር የለም ይላሉ ወጣቱ ሰዓሊ፡፡

አንባቢዎቻችን ቀጣዩን ስዕል ተመልክታችሁ ምን እንደሚናገር ወይም ምን እንዳነበባችሁና ምን እንደተገነዘባችሁ ለራሳችሁ እንድትነገሩ በመጋበዝ ከሰዓሊ ዳዊት ጋር ሞቅ ደመቅ አድርገን የያዝነውን ቃለ ምልልስ አስቀጥለነዋል፤ አሁንም ተከተሉን፡፡

ለሰዓሊ ዳዊት ቀጥለን ያነሳንለት ጉዳይ የስዕል ጥበብ ቀደምት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የጥበብ ዘርፉን ከመምራት ይልቅ ከኋላ የመከተል ሁኔታ ይታይበታል እና ይህ ለምን ሆነ የሚለው ነበር፡፡ ከዚህ አንጻር ሲያብራሩ፡- የስዕል ጥበብ ሙሉ በሙሉ ከኋላ ይከተላል ለማለት አይቻልም፡፡ ጉዳዩን በዘመን ከፋፍሎ ማየት ያስፈልጋል፡፡ በአለም ደረጃ የስዕል ጥበብ ወርቃማ ዘመን ይባል የነበረው ከ14ኛው እስከ 17ኛው ክፍለ ዘመን የቆየው የአውሮፖውያን የስዕልና ስነ-ጽሁፍ ዳግም ልደት (ሬኔይሳንስ) ዘመን ነው፡፡ ያ ዘመን ስነ ስዕል ሌሎችን የጥበብ ዘርፎች እየመራ የዕድገት ማማ ላይ ደርሶ እንደነበር ታሪክ ይናገራል፡፡ ዛሬ ድረስ አለምን ያስደመሙ “የመጨረሻው እራት” እና “ሞና ሊዛ” የመሳሰሉት የስዕል ስራዎችና እነዚህን ስዕሎች የሳሉ እነሊዮናርዶ ዳቬንችን የመሰሉ አንቱ የተባሉ ሰዓሊዎች የነበሩበት ዘመን ሆኖ ተመዝግቧል፡፡

ከዚህ ዘመን በኋላም ቢሆን በምዕራቡ ዓለም የስዕል ጥበብ መተዳደሪያ ሙያ ሆኖ ከፍተኛ ገቢና የስራ እድል መፍጠር የቻለ ትልቅ




በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሚሳሉ ክርስቲያናዊ ስዕሎች መካከል አንዱ

ኢንዱስትሪ ነው፡፡ ነገር ግን ሙዚቃና ፊልሙ ገዝፈው ስለሚደመጡና ስለሚታዩ የስዕል ጥበቡን ዘርፍ ከኋላ የሚከተል አስመስሎታል፡፡

ከኢትዮጵያ ሁኔታ ጋር አያይዘው ሲያብራሩ ደግሞ የስዕል ጥበብ ለኢትዮጵያውያን እንግዳ አይደለም። ዘመናዊ የአሳሳል ጥበብ የሚባለው ሳይተዋወቅ አስቀድሞ፣ ሰዓልያኑ ቀለምን ከቅጠላ ቅጠል አዘጋጅተው፣ በግድግዳዎችና በብራና ላይ ሲጠበቡ ኖረዋል። ስዕልን መተረኪያ ፣ የጽሑፎቻቸው ማብራሪያና ማድመቂያም አድርገው ተገልግለውበታል። የስዕል ጥበብ የሶስት ሺህ ዘመን ታሪክ እንዳለውና በተለይ ከአራተኛው እስከ 12ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ በነበረው የነገስታት ዘመን ክርስትና መንግስታዊ ሀይማኖት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚሳሉ ክርስቲያናዊ ስዕሎች ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቷቸው ይሳሉ ነበር፡፡ በኋላም ክርስትና ይበልጥ እየተስፋፋ በመጣበት ከ14ኛው ክፍለ ዘመን አንስቶ ክርስቲያናዊ ስነ-ስዕል አብሮ ዳብሯል፡፡ ለዚህ የስዕል ጥበብ እድገት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ከፍ ያለ ሚና ተጫውታለች፡፡ በእነዚህ ዘመናት የስዕል ጥበብ (ምንም እንኳን አለማዊ ባይሆንም) ሌሎቹን የጥበብ ዘርፎች መርቷል ማለት ይቻላል፡፡

ቀጥሎም ዘመናዊነትን በኢትዮጵያ ለማስፋፋት በተለይ አፄ ሚኒሊክ ከዚያም አፄ ሀይለ ስላሴ ኢትዮጵያውያንን ወደ ምዕራቡ አለም በመላክ የስዕል ጥበብን ጨምሮ በሌሎችም የጥበብ ዘርፎች ተምረው እንዲመጡ አድርገዋል፡፡ ለአብነት ገብረ ክርስቶስ ደስታ፣የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ፣ የክብር ዶ/ር ሎሬት ለማ ጉያ እና ሌሎችም የስዕል ጥበብን ተምረው ዘርፉን አለማዊና ዘመናዊ መልክ ይዞ እንዲያብብ ብዙ ጥረዋል፡፡ እነዚህ አንጋፋ ሰዓሊያን አለም ክብርና ሞገስ በቸራቸውና አንቱታን ባተረፉባቸው አለማዊ ስዕሎች ቀለም በጥብጠው ሸራ ወጥረው ሀሳብና ተፈጥሮን በጥበባቸው ተራቀውባቸዋል፡፡ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ በመስታወት ላይ የተሰሩ ስዕሎች እንዲሁም የክቡር ዶ/ር ሎሬት ለማ ጉያ ደግሞ በቆዳ ላይ የሰሯቸውን ስዕሎች መጥቀስ እንደሚቻል ሰዓሊው አብራርተዋል፡፡

ከዚየስ? የሚለውን ጥያቄ ለሰዕሊ ዳዊት ስናቀርብላቸው ይህ ቅርብ ወደሆነውና አሁን ላይ የስዕል ጥበብ በምን ደረጃ ላይ ነው ያለው የሚለውን ለመመልከት የሚያስችል ነው፤ካሉ በኋላ በአሁኑ ወቅት የስዕል ጥበብ ጎልቶ ወጥቷል ለማለት አያስደፍርም፡፡ እንደ ሙዚቃና ፊልም ተደራሽ አልሆነም፡፡ ባለበት ቦታ ላይ ደግሞ አልቆመም፡፡ በአማራ ክልልም ይሁን በኢትዮጵያ ትላልቅ ከተሞች ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ሰዓሊያን የስዕል አውደ ርዕይ በበዓላት ቀን ያሳያሉ፡፡ ጋላሪ፣ስቱዲዮና ማዕከል በግለሰብ ደረጃና በማህበር በመደራጀት እየተንቀሳቀሱ ያሉ ሰዓሊዎች ቁጥርም የሚናቅ አይደለም፡፡ እነዚህ እንቅስቃሴዎች በከተሞች አካባቢ ስለሚካሄዱ ስዕል ደረጃው አድጎ መሪ ዘርፍ ሆኗል ባይባልም እንኳ እስትንፋሱ አለ፡፡

በወረዳ ከተሞችና በገጠር አካባቢ ስዕል ያን ያህል ህዝቡ የሚያውቀው፣የሚዝናናበትና የሚሳተፍበት ጥበብ ሆኖ አይታይም፡፡ በእርግጥ ስዕል ከኢትዮጵያዊያን ጋር አብሮ የኖረ ጥበብ ነው፡፡ ገጠር በቤታቸው ግድግዳ ላይ በአመድና በቀይ አፈር የሰው፣የእንሰሳትና የዱር አውሬዎችን ይስሉ ነበር፡፡ ይህን የሚያስቀጥል ስርዓት ስላልተበጀለት ዛሬ ላይ ያለ አይመስለኝም፡፡ በመሆኑም ህዝብ በደንብ አውቆት ተጠቃሚዎችና ተመልካቾች እንዲበዙ ስላልተደረገ ተደራሽነቱ ላይ ክፍተት ተፈጥሯል፡፡

የስዕልን የእድገት ደረጃ ሌላው መለኪያ መንገድ ትልቅ የጥበብ ኢንዱስትሪ ሆኖ ብዙ ገቢ የሚያስገኝ መተዳደሪያ ሙያ ነው ወይ የሚለው ይሆናል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲገመገም እንደ አገርም ይሁን እንደ ክልል ገና ብዙ ይቀረዋል፡፡ ዛሬ ላይ ስዕል ሰርቶ ገቢ እያገኘ የሚተዳደረው ህዝብ ቁጥር ጥቂት ነው፡፡ እንደ ሙዚቃና ፊልም ብዙ የስራ እድልና ገቢ አያስገኝም፡፡ አንጋፋም ይሁን ወጣት ሰዓሊያን ሲስሉ ወይም ሲሞነጫጭሩ የሚታዩት የጥበቡ ፍቅር ስላለባቸው ነው እንጅ ገቢ የሚያገኙበት መተዳደሪያቸው ስለሆነ አይደለም፡፡ ከዚህ አንጻር የስዕል ጥበብ ለባለሞያዎች የሚሰጠው ምጣኔ ሀብታዊ ፋይዳ እዚህ ግባ የሚባል ባለመሆኑ የዘርፉ ክፍተት መሆኑን ሰዓሊ ዳዊት ጠቁመዋል፡፡

ለመሆኑ ስነ ስዕል በዚህ ልክ ደረጃው እንዳያድግ ወይም መሪ የጥበብ ዘርፍ እንዳይሆን ያደረገው ምንድን ነው ብለን ለሰዓሊ ዳዊት ቀጥሎ ያቀረብንላቸው ሌላው ጥያቄ ነው፡፡ ይህን ያብራሩትም 'ተግዳሮቶች' ናቸው ያሏቸውን በመዘርዘር ነበር፡፡ አንዱ ተግዳሮት ትኩረት ያልተሰጠው ዘርፍ መሆኑ ነው፡፡ መንግስት ጥበቡ



ሞና ሊዛ ፡- ስዕል በዘመነ ዳግማዊ ልደት ወቅት የደረሰበትን የእድገት ማማ የሚያሳይ ስራ

ይጠቅመኛል፤ ያስፈልገኛል ብሎ ሰፊ የስራ እድል በሚፈጥር እና ከፍተኛ ግብር ሊያስገኝ በሚችል መልኩ አልመራውም፡፡ ለስዕል ጥበብ ቅርብ የሆነና የሚመለከተው እንደ ባህልና ቱሪዝም ያለ የመንግስት ተቋም ዘርፉን በጥብቅ ዲስፕሊን መከታተልና መደገፍ ላይ ውስንነት አለ፡፡ በቂ በጀትና በዘርፉ ሰፊ እውቀትና ችሎታ ያለውን ባለሙያ መድቦ ማሰማራት ላይ አልተሰራም፡፡

በትምህርት ስርዓቱ ውስጥ ተካቶ እንደሌሎች የቀለም ትምህርቶች አለመሰጠቱም ሌላው ተግዳሮት ነው፡፡ የስዕል ፍላጎትና ዝንባሌ ላላቸው በአጠቃላይ ስዕል መክሊታቸው የሆኑ ተማሪዎች መንገዳቸውን ስተው ባልፈለጉት ዘርፍ እንዲሰማሩ ያደርጋቸዋል፡፡ ይህ ደግሞ ወደ ስዕል ጥበቡ የሚቀላቀሉ ተተኪ ሰዓሊዎችን ስለ ሚያስቀር በሂደት ዘርፉን ባለሙያ አልባ አድርጎ የቀደምትነቱን ያህል የጥበብ ዘርፉን መምራት ሲገባው ከኋላ እንዲከተል አስገድዶታል ፡፡

ዘመናዊው ዲጅታል ፕሪንት ቴክኖሎጅ በራሱ የስዕል ጥበቡን ተፈጥሯዊ ባህሪ እንዲያጣ በማድረግ እየተገዳደረው መሆኑ ይስተዋላል፡፡

በቆርጦ ቀጥል ስልት ከተለያዩ ፎቶዎች እየተወሰዱ የሚሰሩት ስራዎች ነባሩን የስእል ጥበብ እየገደለው፣ ሰዐሊያንንም ዋጋ እያሳጣቸውና እያሰነፋቸው በመሆኑ ጥበቡን የሚፈታተን ተግዳሮት ሆኗል፡፡

ጥበቡ በትውልድ ቅብበሎሽ በአግባቡ እንዲሸጋገር የሚመራበት ስርዓት አለመኖሩም ተጨማሪ ተግዳሮት ሆኖበታልም፤ ይላሉ ሰዓሊ ዳዊት፡፡ የስዕል ጥበብ ከዋሻ ዘመን ጀምሮ እስከዚህ ዘመናዊ ዘመን የደረሰው በትውልዶች መካከል ቅብብሎሽ እንዲኖር የሚያስችል መደበኛ ስርዓት ተዘርግቶለት እየተመራ ነው ለማለት አያስደፍርም፡፡ የስዕል ጥበብ ኢ-መደበኛ በሆነ ቅብብሎሽ እየወደቀ እየተነሳ ነው አሁን ላይ የደረሰው፡፡ በተለይ ክርስቲያናዊ ስዕል አዘውትራ እየተጠቀመች ያለችው የኢትዮጵያ ቤተ-ክርስቲያን ኢ-መደበኛ በሆነው መንገድም ቢሆን ቅብብሎሹ እንዲቀጥል አድርጋለች፡፡ ከዘመናዊ ትምህርት አንጻር ደግሞ በደርግ ዘመን ስነ ስዕል በመደበኛ ሁኔታ በስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ ተካቶ ይሰጥ ነበር፡፡ ቀጥሎ የመጣው ኢህአዴግ የስዕል ጥበብን ቅብብሎሽ በአግባቡ የሚያሻግር የትምህርት ስርዓት አልነበረውም፡፡

በአለማዊው የስዕል መንገድም ቢሆን በራሳቸው ፍላጎትና ጥረት ወደ ስዕል ጥበቡ ገብተው ሰዓሊ በሆኑ ግለሰቦች በጎ አሳቢነት ጥበቡን ለቀጣዩ ትውልድ ለማቀበል በመኖሪያ ቤታቸው ወይም ደግሞ በተከራዩት ጠባብ ስቱዲዮና ጋለሪ የጥበቡ ፍላጎት ላላቸው ውስን ሰዎች ኢ-መደበኛ ስልጠና በመስጠት በኩል ሲሞካከሩ ይታያል፡፡ የስዕል አውደ-ርዕዮችን በማዘጋጀትም ጥበቡን የሚያውቅና የሚያደንቅ የስዕል ቤተሰብ በመፍጠር ቅብብሎሹ ህዝባዊ መሰረት እንዲይዝ አልመው የሚንቀሳቀሱ ሰዓሊያንም አሉ፡፡

ከላይ ከተገለጹት ተግዳሮቶች በተቃራኒ እንደ ኢትዮጵያም ይሁን እንደ አማራ ክልል ለስዕል ስራ ምቹ ሁኔታዎች እንዳሉ መታወቅ አለበት፡፡ አንዱ ምቹ ሁኔታ በርካታ የቱሪስት መስህቦች መኖራቸው ነው፡፡ የስዕል ጥበብና ቱሪዝም ጥብቅ ትስስር ያላቸው ኢንዱስትሪዎች ናቸው፡፡ የቱሪዝም ዘርፉ ከሚተዋወቅባቸው መንገዶች አንዱ ስነ ስዕል ነው፡፡ በአማራ ክልል አሉ የሚባሉትን መስህቦች በስዕል አውደ ርዕይ በማሳየት ክልሉ ያለውን አቅም ለህዝብና ለአለም በማስተዋወቅ የቱሪስቶችን ቁጥር መጨመር ይቻላል፡፡ የቱሪስት ጉብኝቶችንም ከስዕል አወደ ርዕይ ጋር ለማያያዝ ያመቻል፡፡

ለስዕል ስራ መነሻ የሚሆኑ ሀሳቦችና ጭብጦች ክምችት ያለበት ክልልና አገር መሆኑም እንደ ተጨማሪ ምቹ ሁኔታ የሚወሰድ ይሆናል፡፡ ሰዓሊዎች በርካታ ጭብጦችን በስዕሎቻቸው ለመግለጽ አማራጫቸውና እይታቸው ይበዛል፡፡ ክልሉ ትልቅ የሰው ሀብት ስላለው ጥበቡን አውጥቶ ተደራሽ ማድረግ ከተቻለ የሚከተል፣የሚያደንቅና የሚመለከት የስዕል ቤተሰብ መፍጠር ያስችላል፡፡ የሚፈጠረው የስዕል ቤተሰብ ደግሞ ጥበቡ እንዲያድግና እንዲስፋፋ እንዲሁም ቀጣይነት ባለው የትውልድ ቅብብሎሽ እንዲሻገር ያደርገዋል፡፡



የክቡር ዶ/ር ሎሬት ለማ ጉያ በቆዳ ላይ ከሳሏቸው ስዕሎች መካከል አንዱ

የዘመኑን ዲጅታል ፕሪንቲንግ ቴክኖሎጅ በአግባቡ መጠቀም ከተቻለ ጥበቡን ለማዘመን አመች ነው፡፡ ቴክኖሎጅው ስዕል ተፈጥሯዊ ባህሪውን ሳይለቅ የአሳሳል ስልት እውቀትን ያስጨብጣል፡፡ የስዕል ፍላጎትና ዝንባሌ ያላቸው ሰዎች የቴክኖሎጅውን በጎ ጎን በመከተል ስዕል እንዴት እንደሚሳል አቅጣጫ ከሚያሳዩ በርካታ ቴክኒካል ጉዳዮች ጋር እንዲተዋወቁ ያግዛቸዋል፡፡ ከቴክኖሎጅው የሚወስዱትን እውቀት እርሳስ፣ ብሩሽ፣ ወረቀት፣ ሸራና ቀለም ተጠቅመውና የራሳቸውን እይታ ጨምረውበት ለሚስሉ ሰዓሊያን ጥሩ አጋዥ ስለሚሆን በጥንቃቄ ሊጠቀሙበት እንደሚገባ አመላክተዋል ሰዓሊ ዳዊት፡፡

በአጠቃላይ ስነ-ስዕል አገራዊ ፍቅርና ታሪኮችን ያቆየ፣ከማንነት ጋር ጥብቅ ቁርኝነት ያለው ጥበብ ነው፡፡ በስዕል የተቀመጡ የጥንት ማንነቶች፣ ታሪኮች፣ ወዘተ. ዜጎች በአገራቸው እንዲኮሩና እንዲደሰቱ ያደርጋል፡፡ ስለሆነም የስዕል ጥበብ ባይኖር ኖሮ ይህን ሁሉ ታሪካሚና ሞራላዊ እሴት ማግኘት አይቻልም ነበር፡፡ የኢትዮጵያ የሶስት ሺህ ዓመት ታሪክ በሙሉ ባለመፃፉ ያን ታሪክ በስዕል ጥበብ በተለይም ክርስቲያናዊ ስዕሎች ከሞላ ጎደል አባይን በጭልፋ እንደሚባለው ጨልፈው አስረክበውናል፡፡ የስዕል ጥበብ ለታሪክ ቀጣይነት ትልቅ ዋስትና ስለሆነ ከአለም ጋር ያለውን ትስስር ያዳብራል፡፡ በመሆኑም የስዕል ጥበብ ፋይዳው ይህን ያህል ሰፊ ከሆነ ቀጣይነቱ ተጠብቆ አገልግሎቱ እንዲበዛ ምቹ ነገሮች ሊፈጠሩለት እንደሚገባ ሰዓሊው ይመክራሉ፡፡

በመጨረሻ ለሰዓሊ ዳዊት ያቀረብንላቸው ጥያቄ ከላይ በተገለፀው መልኩ የስዕል ጥበብ ካጋጠመው የመረሳት፣ትኩረት የማጣትና የመደፈቅ አደጋ ተላቆ ውስጣዊ ደስታንና እርካታን የሚሰጥ፣ሰፊ የስራ እድል የሚፈጥር፣ ገቢ የሚያስገኝ ሙያ እንዲሆን እና ከሌሎች ዘርፎችም ጋር የሚወዳደር ኢንደስትሪ ሆኖ እንዲወጣ ከማን ምን ይጠበቃል የሚለው ነበር፡፡ እሳቸውም ሲያብራሩ ከግል ባለሀብቶች፣ ከጥበቡ ባለሙያዎች፣ከማህበረሰቡ እና ከመንግስት ብዙ ይጠበቃል፡፡

የግል ባለሀብቶች ኢንቨስት ቢያደርጉበት መልካም ነው፡፡ ዘርፉን በደንብ በማነቃቃት በኩል ባለሀብቶች የተሻለ የገንዘብ አቅም ስላላቸው የጥበቡን ህልውና በማስቀጠልና ለትውልድ በማሻገር፣ተወዳጅነቱ እንዲያንሰራራ በማድረግ፣ እንደ አገርና ክልል ገጽታን በመገንባትና ምጣኔ ሀብትን በማሳደግ በኩል ሚናው የላቀ ይሆናል፡፡ የጥበቡን ባለሙያዎች በተሻለ መልኩ በማሳተፍ የዘርፉን የስራ ጥራት በሚገባው ልክ እንዲጠበቅም ያደርገዋል፡፡

የጥበቡ ባለሙያዎች ወይም ሰዓሊዎች ከእነሱም ብዙ እንደሚጠበቅ አውቀው ጥበቡ አንገቱን ደፋ ብለው በተስፋ መቁረጥ ስሜት መቆዘም የለባቸውም፡፡ በግልም ይሁን በማህበር ተደራጅተው በመቆም ዘርፉ እንዲያንሰራራ፣ ተቀባይነቱ እንዲጨምር ጠንካራ ተጋድሎ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ በየከተሞች ለማስታወቂያነትና ለድርጅቶች ሎጎ ተብለው በዲጅታል ፕሪንት ቴክኖሎጅ እየተቀናበሩ የሚሰሩት ስራዎች ነባሩን ስነ-ስዕል እየጎዱት መሆኑንም አውቀው ሰዓሊዎች ይህም ከሚደርጉት አካላት ጋር ተገናኝቶ በመስራት እውነተኛውን የስዕል ውበትና እርካታ ለስዕል አፍቃሪያን ማሳየት እንዲቻል ሁለንተናዊ ክትትል ማድረግ አለባቸው፡፡

ህብረተሰቡ በተለይ ወላጆች የስዕል ፍላጎትና ዝንባሌ ያላቸውን ልጆቻቸውን ስሜት ማዳመጥና ጥበቡን እንዲቀምሱትና እንዲኖሩበት በቤታቸው የስዕል ቁሳቁሶችን ማሟላት አለባቸው፡፡ እንደሚታወቀው በክልላችን ብዙም የስዕል ትምህርት ቤቶች ስለሌሉ ልጆች የስዕል ፍላጎታቸውንና ዝንባሌያቸውን ሊገልጹበት የሚችሉበት እድል የላቸውም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ወላጆች ልጆቻቸውን በግልም ይሁን በማህበር በተደራጁ የስዕል ስቱዲዮዎች አጫጭር ስልጠናዎች የሚሰጡበት ሁኔታ ስላለ ወደዚያ በመላክ የወደፊት መስመራቸውን ማሳየት መቻል ይኖርባቸዋል፡፡ ወጣቶችና ተማሪዎችም የስዕል አውደ-ርዕዮችን የሚያዘጋጁ ሰዓሊያንን በቦታው እየተገኙ ማበረታታት፣ ማድነቅ፣ ወዘተ. .ይገባቸዋል፡፡

መንግስትም ስነ- ስዕል በስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ በደንብ ተካቶ ተማሪዎች እንደ አንድ የትምህርት አይነት እንዲማሩት በማድረግ የወደፊት መክሊታቸውን እንዲያገኙት ከማድረግም ባሻገር ተተኪ ባለሙዎችን ለማፍራት ያስችላል፡፡ ጥበቡ እንዲያንሰራራ መንግስት ትኩረት ሰጥቶት ሰዓሊያን የሚበረታቱበት አሰራር ቢፈጥር ሁሉም ተጠቃሚ እንደሚሆን ጠቁመዋል፡፡

ሰዓሊ ዳዊት በመልዕክታቸው የስዕል ጥበብ አሁን ላይ የሁላችንም እርዳታ በተለይ ደግሞ ለጥበቡ ቅርበት፣ፍቅርና ፍላጎት ያላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ይፈልጋልና አለንልህ ልንለው ይገባል፡፡ የትምህርት ተቋማትና ምሁራን ድምጻቸውን ያሰሙ፤ወደ ቀደመ ህልሙናው ለመመለስም እንረባረብ፤በማለት አስተላልፈው ሀሳባቸውን ቋጭተዋል፡፡

እኛም ስነ ስዕል እንደ አለም ከነበረው ቀደምት ሰፊ ታሪክ ላይ በትንሹ በመጨለፍ በአሁኑ ወቅት እንደ ኢትዮጵያና አማራ ክልል ያለበትን ደረጃ፣ ፋይዳና እንቅስቃሴ በሚመለከት የዳሰስንበትን ዝግጅት በዚህ ቋጨን- ሰላም፡፡








የባህርዳር ዓለም አቀፍ ስታዲየም ግንባታ ሂደት


Processing Fact
Responsibilit
1. Support Student
2. Support School
3. School Building
4. Support People
5. University-Indu
6. Participate in th
Championship
7. Other supports
ELFORA


RIKUM HOTEL